# የብልፅግና ፓርቲ (ብልፅግና)
# መተዳደሪያ ደንብ

**(ረቂቅ)**

**ታህሳስ 21 ቀን 2017 ዓ.ም**
**ብልፅግና ፓርቲ ዋና ጽ/ቤት**
**አዲስ አበባ**

# ማውጫ


መግቢያ 1
ጠቅላላ ድንጋጌዎች 2
አንቀጽ አንድ - አጭር ርእስ 2
አንቀጽ ሶስት - የፓርቲው መጠሪያ 5
አንቀጽ አራት - የፓርቲው ዓርማ 5
አንቀጽ አምስት - የፓርቲው የሥራ ቋንቋዎች 6
አንቀጽ ስድስት - የፓርቲው ልሳን 6
አንቀጽ ስምንት - የፓርቲው ዓላማዎች፣ መርሆች፣ ዕሴቶችና የአሠራር ሥርዓቶች 6
አንቀጽ ዘጠኝ - የፓርቲው ምርጫ መርህና የአሠራር ሥርዓት 10
7. የአስመራጭ ኮሚቴው የሚከተሉት ተግባራት እና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡ 11
አባልነት 12
አንቀጽ አስር - የፓርቲው አባል ስለመሆን 12
አንቀጽ አስራ አንድ - ለአባልነት የሚቀርብ ጥያቄ 12
አንቀጽ አሥራ ሁለት - የአባል መብት 13
አንቀጽ ዐሥራ አራት - የአባልነት ግዴታ 14
አንቀጽ ዐሥራ አምስት - በአባላት ላይ በዲሲፐሊን ጉድለት ስለሚወሰዱ እርምጃዎች 15
የፓርቲው አወቃቀርና አደረጃጀት 17
አንቀጽ ዐሥራ ስድሰት - የፓርቲ አወቃቀርና የአመራር አካላት 17
አንቀጽ ዐሥራ ሰባት - የፓርቲው ጉባኤ፣ የክልል፣ አዲስ አበባና ድሬዳዋ፣ የዞን፣ የከተማ፣ የወረዳና የቀበሌ የኮንፈረንሶች አወቃቀር 18
አንቀጽ ዐሥራ ስምንት - የፓርቲው ጉባኤ 18
አንቀጽ ዐሥራ ዘጠኝ - የፓርቲው ጉባኤ ተግባርና ኃላፊነት 20
አንቀጽ ሃያ - የፓርቲው የብልፅግና ምክር ቤት 20
አንቀጽ ሃያ አንድ - የፓርቲው ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ 22
አንቀጽ ሃያ ሁለት - የፌዴራልና የክልል ፓርቲ አመራሮች የጋራ መድረክ 24
አንቀጽ ሃያ ሶስት - የፓርቲው ፕሬዝዳንት 24
አንቀጽ ሃያ አራት - የፓርቲው ምክትል ፕሬዝዳንቶች 24
አንቀጽ ሃያ አምስት - የፓርቲው ማዕከላዊ የኢንስፔክሽንና የሥነ-ምግባር ኮሚሽን 25
አንቀጽ ሃያ ስድስት - የፓርቲው ዋና ጽ/ቤት 28
የፓርቲው የክልል አደረጃጀት 29
አንቀጽ ሃያ ሰባት - የፓርቲ አደረጃጀትና አወቃቀር 29
አንቀጽ ሃያ ስምንት - የክልል፣ አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋና የፌዴራል ተቋማት ፓርቲ ኮንፈረንስ የአሠራር ሥርዓት 30
አንቀጽ ሃያ ዘጠኝ - የፓርቲ ኮንፈረንስ ተግባርና ኃላፊነት 31
አንቀጽ ሠላሳ - የክልሎች፣ የአዲስ አበባና የድሬዳዋ እንዲሁም የፌዴራል ተቋማት የፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ 31

አንቀጽ ሠላሳ አንድ - የየደረጃው ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች 32
አንቀጽ ሠላሳ ሁለት - የብልጽግና ፓርቲ የሴቶች ክንፍ 33
አንቀጽ ሠላሳ ሶስት - የብልጽግና ፓርቲ የወጣቶች ክንፍ 34
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች 35
አንቀጽ ሠላሳ አራት - የሥልጣን ዘመን 35
አንቀጽ ሠላሳ አምስት - የፓርቲው የፋይናንስ ምንጮች 36
አንቀጽ ሠላሳ ስድስት - የፓርቲው የሀብት አስተዳደርና የሂሳብ መዛግብት የአሠራር ሥርዓት 36
አንቀጽ ሠላሳ ሰባት - በፓርቲው ውስጥ የሚፈጠሩ አለመግባባቶች አፈታት ሥርዓት 36
አንቀጽ ሠላሳ ስምንት - የፓርቲው ውሕደት፣ ቅንጅት ወይም ግንባር የመፍጠር ሥርዓት 36
አንቀጽ ሠላሳ ዘጠኝ - የፓርቲው መፍረስ 37
አንቀጽ አርባ - የፓርቲው የአሰላሳይ ቡድን 37
አንቀጽ አርባ አንድ - የፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ የበላይነት 37
አንቀጽ አርባ ሁለት - መመሪያ የማውጣት ሥልጣን 37
አንቀጽ አርባ ሶስት - መተዳደሪያ ደንቡን ስለማሻሻል፣ መቀየር እና ስለመሻር 38
አንቀጽ አርባ አራት - መተዳደሪያ ደንቡ ስለሚጸናበት ሁኔታ 38

**መግቢያ**

እኛ የብልፅግና ፓርቲ አባላት የሀገራችን ኢትዮጵያን ዕድገትና የጋራ ብልፅግና እውን ለማድረግ በመነሣት፣

ሀገራችንን ወደሚቀጥለው ምእራፍ ለማሻገር አዲስ ራእይና አዲስ ትርክት እንደሚያስፈልግ በማመን፣

የሕግ የበላይነትና ዴሞክራሲ የሰፈነባት፣ የግለሰብና የቡድን መብቶች በሚዛኑ የሚከበሩባት፣ ዜጎች ከድህነት ተላቀው በብልጽግና የሚኖሩባት፣ ጠንካራና ቀጣይ የኢኮኖሚ ዕድገት የሚታይባት፣ በቀጣናዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊው መድረክ ላይ ጉልህ ሚና የሚትጫወት ኢትዮጵያን ለማየት ባለን ተስፋ፣

የበለፀገች፣ ኅብረ-ብሔራዊ ማንነቷ የዳበረና አንድነቷ የተጠናከረ ኢትዮጵያን ዕውን ለማድረግ ባለን ቁርጠኝነት፣

ይህንንም ለመተግበር በመደመር አስተሳሰብና በአንድነት ቅኝት በመነሣት፣ ልናያት የምንፈልጋትን ኢትዮጵያ ለመገንባት የእያንዳንዳችንን ርብርብ የሚጠይቅ መሆኑን በመረዳት፣ የበኩላችንን ሚና ለመጫወት በከፍተኛ ቆራጥነት ተሰባስበን መታገል በማስፈለጉ፣

የብልፅግና ፓርቲ የሚመራበት የመተዳደሪያ ደንብ በመጀመሪያ ጉባኤ ጸድቆ ሥራ ላይ የነበረው በአፈጻጸም ላይ ከታዩት ጉዳዮች በመነሳት ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣ ይህ መተዳደሪያ ደንብ በኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነ ምግባር ዐዋጅ ቁጥር 1162/2011 የተደነገጉትን ሕጎች የሚያከብር የብልፅግና ፓርቲ (ብልፅግና) ሰነድን በሁለተኛ ጉባኤያችን መክረንበት ሕጋዊ የፓርቲውን ሰነድ አድርገን አጽድቀናል።

## <u>ምእራፍ አንድ</u>

## <u>ጠቅላላ ድንጋጌዎች</u>

**አንቀጽ አንድ - <u>አጭር ርእስ</u>**

**ይህ መተዳደሪያ ደንብ "የብልፅግና ፓርቲ (ብልፅግና) መተዳደሪያ ደንብ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።**

**አንቀጽ ሁለት - <u>ትርጓሜ</u>**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም በሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ

1. **"ፓርቲ"** ማለት ብልፅግና ፓርቲ /ብልፅግና/ ማለት ነው፡፡
2. "ጉባኤ" ማለት የፓርቲው ከፍተኛ አመራር አካል ነው፡፡
3. **"ፕሮግራም"** ማለት በፓርቲ አንደኛው ጉባኤ ያፀደቀው የፓርቲ የፕሮግራም ነው፡፡
4. **"መተዳደሪያ-ደንብ"** ማለት በፓርቲ ሁለተኛው ጉባኤ ተሻሽሎ ያፀደቀው የፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ ማለት ነው፤
5. **"የብልፅግና ምክር ቤት"** ማለት በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ከጉባኤ እስከ ጉባኤ ፓርቲውን የሚመራ ከፍተኛ የብልጽግና ፓርቲ አካል ነው፤
6. **"ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ"** ማለት በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ከማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት መካከል የሚመረጡ የፓርቲ ጉባዔና የማዕከላዊ ኮሚቴ የተወሰኑ ውሳኔዎች አስፈጻሚ አካል ነው፡፡
7. **"ፕሬዚዳንት"** ማለት የብልፅግና ፓርቲ ፕሬዚዳንት ነው፡፡
8. **"ምክትል ፕሬዚዳንቶች"** ማለት የብልፅግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዚዳንቶች ናቸው፡፡
9. **"ኮሚሽን"** ማለት በዚህ መተዳደሪያ ደንብ የተቋቋመ በየደረጃው የሚገኘው የፓርቲው የኢንስፔክሽንና የሥነ-ምግባር ኮሚሽን ማለት ነው፤
10. **"ዋና ኮሚሽነር"** ማለት የብልፅግና ፓርቲ የኢንሰፔክሽንና የሥነ-ምግባር ዋና ኮሚሽነር ነው፡፡
11. **"ምክትል ኮሚሽነር"** ማለት የብልጽግና ፓርቲ የኢንሰፔክሽንና የሥነ-ምግባር ምክትል ኮሚሽነር ነው፡፡
12. **"ዋና ጽህፈት ቤት"** ማለት የብልፅግና ፓርቲ ዋና ጽህፈት ቤት ነው፡፡

13. **"ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት"** ማለት ከክልል እስከ ቀበሌ ባሉ መዋቅሮች የተቋቋመ የብልፅግና ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ማለት ነው::

14. **"ክልል"** ማለት በህገ መንግሥቱ አንቀጽ 47 መሠረት የተቋቋመ ክልል ሲሆን ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ሲባል የአዲስ አበባ ከተማ እና የድሬዳዋ አስተዳደርን ይጨምራል።

15. **"ዞን"** ማለት ለክልል ተጠሪ የሆኑ የዞን አስተዳደሮች፣ የአዲስ አበባ ክፍለ ከተሞች እና በዞን ደረጃ ያሉ ከተሞችን እና ልዩ ወረዳዎችን የሚያጠቃልል ነው።

16. **"ወረዳ"** ማለት በክልሎች፣ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የወረዳ ደረጃ የተሰጣቸው የአስተዳደር አካላትን ያጠቃልላል።

17. **"አስተባባሪ ኮሚቴ"** ማለት የፓርቲና የመንግስት ሥራዎችን አቀናጅቶ በበላይነት የሚያስተባብር እና በፓርቲው የበላይ አካላት የሚተላለፉ ውሳኔዎችና መመሪያዎች ተግባር ላይ መዋላቸውን የሚያረጋግጥ በየደረጃው የሚገኝ የፓርቲው አደረጃጀት ነው።

18. **"የፓርቲ አመራር ኮሚቴ"** ማለት በፓርቲ ዋና ጽ/ቤት እና በየደረጃው በሚገኙ የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የፓርቲ ስራዎችን አቀናጅቶ የሚመራ፣ የሚያስፈጽምና የሚፈጽም የአመራር ኮሚቴ ማለት ነው::

19. **"አመራር"** ማለት የፓርቲውን ፕሮግራም ለማስፈጸም በየደረጃው ባለው የፓርቲው መዋቅሮች በሃላፊነት የተመደበ ወይም የተመረጠ ማለት ነው::

20. "አባል" ማለት የብልፅግና ፓርቲን መተዳደሪያ ደንብ እና ፕሮግራምን ተቀብሎ የአባልነት መብትና ግዴታውን የሚወጣ የፓርቲዉ አባል ማለት ነዉ።

21. "የአባላት ግንባታ" ማለት በየወቅቱ ፓርቲው ከህዋስ ውይይት ጀምሮ እስከ ከፍተኛ አመራር ስልጠና የሚሰጥባቸው የአቅም ግንባታ ስራዎችን የሚያጠቃልል ነው::

22. "የአባላት ስንብት" ማለት አባሉ ከፓርቲው ጋር የነበረው ቆይታ በተለያዩ ምክንያቶች አብቅቶ፤ ከፓርው ጋር የሚለያይበትና ከፓርቲው የሚሰናበትበት ሂደት ነው::

23. "የክብር አባላት" ማለት በፓርቲው ውስጥ ትልቅ አስተዋጽኦ አበርክተው በዕድሜ፣ ወይም በሌሎች አስገዳጅ ሁኔታዎች ወይም በፓርቲው እውቅናና ፍቃድ ከሙሉ አባልነት ወደ ክብር አባልነት ተሸጋግረው የክብር አባልነት እውቅና የሚሰጣቸው አባላት ናቸው::

24. **“ክንፍ”** ማለት የፓርቲው የሴቶችና የወጣቶች አደረጃጀት የወል መጠሪያ ማለት ነው፡፡

25. **“የብልፅግና ህብረት”** ማለት በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የተቋቋመና ሁለት እና ከዚያ በላይ የብልፅግና ቤተሰብን ያቀፈ ማለት ነው፡፡

26. **“የብልፅግና ቤተሰብ”** ማለት በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የተቋቋመና የአባላት የዕለት ተዕለት አቅም የሚገነባበት የፓርቲው የመጨረሻው እርከን የአባላት ስብስብ አደረጃጀት ነው፡፡

27. **”ኮንፈረንስ“** ማለት በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የተቋቋመና በየደረጃው የፓርቲ አባላት በጋራ ሆነው የተግባራት አፈጻጸም ግምገማና የተለያዩ ውሳኔዎችን የሚያስተላልፉበት መድረክ ነው፡፡

28. **‘’ሙሉ አባል’’** ማለት የዕጩነት ጊዜ የጨረሰ እና በብልፅግና ህብረት የአባላት ኮንፈረንስ ወደ ሙሉ አባልነት የተሸጋገረ አባል ነው፡፡

29. **‘’እጩ አባል’’** ማለት የደጋፊነት ጊዜ የጨረሰ እና በብልፅግና ህብረት የአባላት ኮንፈረንስ ወደ ዕጩ አባልነት የተሸጋገረ አባል ማለት ነው፡፡

30. **“ደጋፊ አባል’’** ማለት የብልፅግና ፓርቲ ዓለማዎች፣ እሳቤዎች፣ መርሆዎችና እሴቶችን ተቀብሎ የሚደግፍ ግለሰብ ማለት ነው፡፡

31. **“የአባልነት ክፍያ’** ማለት እያንዳንዱ አባል በራሱ ፍላጎት የፓርቲ አባል በመሆኑ ከሚገኘው ገቢ በቁርጥ ወይም ከደመወዝ በወር ወይም በዓመት የሚከፍለው መዋጮ ነው፡፡

32. **“ቅሬታ’’** ማለት የፓርቲ አባላትና አመራሮች ከፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ እና የአሰራር መመሪያዎች ውጭ በደል ተፈጸመብን ብለው ሲያምኑ በየደረጃው ለሚገኘው የፓርቲ አካላት የሚያቀርቡት ቅሬታ ማለት ነው፣

33. **“አቤቱታ’’ ማለት** በየደረጃው ላለው የፓርቲ መዋቅር ቅሬታ አቅርቦ በውሳኔው ባልረኩ አባላት በየደረጃው ላሉት የኮሚሽን መዋቅር የሚቀርብ አቤቱታ ማለት ነው፣

34. በዚህ መመሪያ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው ሴትንም ይጨምራል፡፡

**አንቀጽ ሶስት - <u>የፓርቲው መጠሪያ</u>**

የፓርቲው መጠሪያ **"የብልፅግና ፓርቲ (ብልፅግና)"** ነው።

**አንቀጽ አራት - <u>የፓርቲው ዓርማ</u>**

1. **የዓርማው ቀለምና አቀማመጥ**

በክብ ነጭ መደብ ውስጥ በስተግርጌ ጥቁር ቀለም ያላቸው ለማቀፍ የተዘጋጁ ሁለት የሰው እጅ ምስሎች ያሉት ሲሆን፣ መሐል ላይ ለማቀፍ የተዘጋጁ የሰው እጆች ምስሉ ውስጥ ሆነው የሚታዩ ሦስት የተለያዩ ቀለማት ያላቸው ሦስት ሰዎች የሚገኙበት ነው። ከዚህ በተጨማሪ ከውስጥ ወደ ውጭ የሚፈነጥቁ ቢጫ ቀለም ያላቸው የብርሃን ፍንጣቂዎችን በውስጡ አካቶ የያዘ ነው።

2. **ጥቅል ትርጉም**

ዓርማው የሀገራችንን ኅብረ ብሔራዊነትን፣ ሀገራዊ አንድነትን፣ ብሔራዊ ኩራትን፣ ሰላምን፣ ዴሞክራሲንና የብልጽግናን አስተሳሰብ የያዘ ሆኖ ከውስጥ ወደ ውጭ እየሰፋ የሚሄድ የቀጣናዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ትሥሥሮችን የሚያመላክት ነው።

3. **ዝርዝር ትርጉም**

**ሀ) እጅ፡-**

በዓርማው (ሎጎው) በስተግርጌ በኩል የተቀመጠው የሰው የእጅ ምስል ብልፅግና ሁሉን አቃፊና አካታች መሆኑን የሚወክል ሲሆን ቀለሙ ጥቁር የሆነበት ምክንያት ኢትዮጵያውያን የጥቁር ሕዝቦች የነጻነትና የድል ተምሳሌት መሆናችንን የሚወክል ነው።

**ለ) የሰዎች ምስል፡-**

ብልፅግና ሰው ተኮር ፓርቲ መሆኑን የሚወክል ሲሆን ፓርቲው ለሰው ልጆች ሁለንተናዊ ብልፅግና የሚታገል መሆኑን ይወክላል። የሰዎቹ ምስል ቀለማቸው ሰማያዊ፣ ቢጫና ሮዝ ሆኖ የተለያየ መሆኑ የኢትዮጵያን ብዝኃነት እንዲያሳይና ብዝኃነታችን የውበታችንና የጠንካራ አንድነታችን ምልክት ሆኖ ተወክሏል።

**ሐ) ጎህ፡-**

ከላይ የተቀመጡት የብርሃን ፍንጣቂዎች ጎህን የሚወክሉ ሲሆን ጎህ ጨለማን ሰንጥቆ የሚመጣ ብርሃን እንደመሆኑ መጠን ብልፅግና ኢትዮጵያን ወደ ከፍታና የብርሃን ዘመን ለማሸጋገር የሚታገል ፓርቲ መሆኑን የሚወክል ነው።

**አንቀጽ አምስት - <u>የፓርቲው የሥራ ቋንቋዎች</u>**

1. ፓርቲው ለሁሉም የሀገራችን ቋንቋዎች ሙሉ ዕውቅና ይሰጣል።
2. በፌዴራል ደረጃ የፓርቲው የሥራ ቋንቋ የሀገሪቱ ሕገ መንግሥት እና ክልሎች በሕገ መንግሥታቸው የሥራ ቋንቋ አድርገው ያጸደቋቸው ቋንቋዎች ይሆናሉ።
3. በየደረጃው የሚገኙ የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የየራሳቸውን ተጨባጭ ሁኔታ ታሳቢ በማድረግ ቢያንስ አንድ የፓርቲውን የሥራ ቋንቋ በተጨማሪነት መጠቀም ይችላሉ።

**አንቀጽ ስድስት - <u>የፓርቲው ልሳን</u>**

1. የፓርቲው ልሳን ***"ብልፅግና"*** ነው።
2. የፓርቲው ልሳን በፓርቲው የሥራ ቋንቋዎች የሚዘጋጅ ብዝኃ ልሳን ነው።
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እንደተጠበቀ ሆኖ በሌሎች የሀገሪቱ እና የውጭ ቋንቋዎች ሊዘጋጅ ይችላል።

**አንቀጽ ሰባት - <u>የፓርቲው ጽሕፈት ቤት</u>**

1. የፓርቲው ዋና ጽሕፈት ቤት አዲስ አበባ/ፊንፊኔ ይሆናል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ፓርቲው በክልል፣ በአዲስ አበባ ከተማና በድሬዳዋ አስተዳደር፣ በከተማ አስተዳደር /በዞን/ በልዩ ወረዳ/በዞን ደረጃ ያሉ ክፍለ ከተሞች፤ በወረዳ/በወረዳ ደረጃ ያሉ ከተሞች/በወረዳ ደረጃ ያሉ ክፍለ ከተሞች እና በቀበሌ ጽሕፈት ቤቶች ይኖሩታል።
3. ፓርቲው እንደ አስፈላጊነቱ በውጭ ሀገር ጽሕፈት ቤቶች ሊያቋቁም ይችላል።

**አንቀጽ ስምንት - <u>የፓርቲው ዓላማዎች፣ መርሆች፣ ዕሴቶችና የአሠራር ሥርዓቶች</u>**

1. **የፓርቲው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፤**

   ሀ) ጠንካራ፣ ዴሞክራሲያዊ፣ ቅቡልነት ያለው፣ ዘላቂ ሀገረ-መንግሥትና ኅብረብሔራዊ አንድነት መገንባት፤

   ለ) ልማትና ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጥ አካታች የኢኮኖሚ ሥርዓት መገንባት፤

   ሐ) ሁለንተናዊ ብልጽግናን የሚያሰፍን ማኅበራዊ ልማትን ማረጋገጥ፤

   መ) ሀገራዊ ክብርንና ጥቅምን ማዕከል ያደረገ የውጭ ግንኙነት ማካሄድ።

2. **የፓርቲው መርሆች የሚከተሉት ናቸው፤**

ሀ) ሕዝባዊነት፣

ለ) ዴሞክራሲያዊነት፣

ሐ) የሕግ የበላይነት፣

መ) ልማትና ፍትሐዊ ተጠቃሚነት፣

ሠ) ተግባራዊ እውነታ፣

ረ) ሀገራዊ አንድነትና ኅብረ ብሔራዊነት።

3. **የፓርቲው ዕሴቶች የሚከተሉት ናቸው፤**

ሀ) የዜጎችና የሕዝቦች ክብር፣

ለ) ነፃነት፣

ሐ) ፍትሕ፣

መ) ኅብረ ብሔራዊ ወንድማማችነትና እኅትማማችነት፣

ሠ) መከባበርና መቻቻል፣

ረ) ኅብረ ብሔራዊ አንድነት፣

ሰ) አሳታፊነትና አካታችነት፣

ሸ) ግልፀኝነትና ተጠያቂነት።

4. **የፓርቲው የአሠራር መርሆዎች የሚከተሉት ናቸው፤**

ሀ) ፓርቲው የሀገሪቱን እና የክልሎችን ሕገ-መንግሥት እና ሌሎች ሕጎችን በማክበር ተግባራቱን ያከናውናል፤

ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (3) የተደነገጉትን ድንጋጌዎች የፓርቲው አባላት የመፈጸም፣ የማክበርና የማስከበር ኃላፊነት አለባቸው፤

ሐ) አባላት የግል ሐሳባቸውን የማራመድ መብታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የፓርቲውን ውሳኔ የመፈጸምና የማስፈጸም ኃላፊነትና ግዴታ አለባቸው፤

መ) ማንኛውም ሙሉ አባል በፓርቲ ውስጥ እኩል ድምፅና በውሳኔ ሂደቶች ውስጥ አንድ ድምፅ ብቻ ይኖረዋል፤

ሠ) የፓርቲ ውሳኔ በየደረጃው ዴሞክራሲያዊ ውይይት ከተካሄደበት እና የጋራ ግንዛቤ ከተያዘበት በኋላ በተባበረ ድምፅ እንዲወሰን ጥረት ይደረጋል፤

ረ) በተባበረ ድምፅ ለመጽደቅ ባልቻሉ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ የሚተላለፈው በአብላጫ ድምፅ ይሆናል። ተፈጻሚነቱም በወሰነው አካል እና በታችኛው መዋቅር ላይ ይሆናል፤

ሰ) በሌላ አኳኋን በዚህ ደንብ ካልተደነገገ በስተቀር የፓርቲው ውሳኔ የሚያልፈው በአብላጫ ድምፅ ነው። የተሰጠው ድምፅ ለሁለት እኩል የተከፈለ ከሆነ ሰብሳቢው ያለበት ወገን ድምፅ አሸናፊ ይሆናል፤

ሸ) በዚህ ደንብ በተለየ አኳኋን ካልተደነገገ በስተቀር የየትኛውም የፓርቲው መዋቅር ምልዐተ ጉባኤ ተሟልቷል የሚባለው ከጠቅላለው የኮንፈረንስ ወይም የስብሰባው ተሳታፊዎች 50%+1 እና ከዚያ በላይ ሲገኙ ነው፤

ቀ) ሁሉም የፓርቲ ሙሉ እና እጩ አባላትና አመራር በብልፅግና ቤተሰብ እና ብልፅግና ህብረት አደረጃጀቶች ተደራጅተው የመንቀሳቀስ እና በየደረጃው በሚካሄዱ ኮንፈረንሶችና ስብሰባዎች የመገኘት ግዴታ አለባቸው፣ ሆነ ብሎ ምልዐተ ጉባኤ እንዳይሟላ ማድረግ የተከለከለ ነው። ምልዐተ ጉባኤ እንዳይሟላ ያደረገ በዲስፕሊን ጥፋት ይጠየቃል፤

በ) በየትኛውም ደረጃ በተወሰነ ውሳኔ ላይ ከተሰብሳቢ አባላት መካከል አንድ ሶስተኛ የሚሆኑት እንደገና እንዲታይ ጥያቄ ካቀረቡ፤ ጥያቄው ለውይይት ክፍት ሆኖ እንደገና ውሳኔ ይሰጥበታል፤

ተ) በአንድ መድረክ ላይ በተወሰነ ውሳኔ ላይ አቤቱታ ቀርቦ ውሳኔው በድጋሚ በዚያው መድረክ ተቀባይነት ካገኘ በድጋሜ አቤቱታ አይቀርብም። በጉዳዩ ላይ አቤቱታ ማቅረብ የሚቻለው በተግባር እየፈጸሙ በሂደት በሚከፈት የጉባኤ ወይም ኮንፈረንስ አጋጣሚ ወይም የጽሑፍ ፊርማ በማሰባሰብ ብቻ ይሆናል፤

ቸ) እንደገና ይታይልን የሚል ጥያቄ ሲቀርብ የወሰነው አካል በጉባኤ ላይ ከሆነ በቃል ወይም በጽሑፍ አቤቱታው ቀርቦ ጉዳዩ ከላይ በተቀመጠው መሠረት ይታያል። ወሳኙ አካል ጉባኤው ወይም ኮንፈረንሱ ወይም ስብሰባው ፈጽሞ ከተበተነ በኋላ ግን አቤቱታ ሊቀርብ የሚችለው በጽሑፍ ብቻ ይሆናል፤

ኀ) አቤቱታ አቅራቢው አቤቱታውን በጽሑፍ አዘጋጅቶ ለሰብሳቢው ያቀርባል። ሰብሳቢው አቤቱታውን ወደሚመለከታቸው አባላት ሁሉ በአጭር ጊዜ ውስጥ በማሠራጨት አቤቱታውን የሚደግፉ ሁሉ እንዲፈርሙ ያደርጋል። ከሚመለከታቸው አባላት ውስጥ አንድ

ሶስተኛው ከፈረሙ፤ ጉዳዩ በሚቀጥለው መደበኛ ወይም አስቸካይ ስብሰባ ላይ እንዲታይ ይደረጋል፤

ነ) ሁሉም የፓርቲው አሠራሮች በግልፀኝነትና ዴሞክራሲያዊነት ላይ የተመሠረቱ ይሆናሉ፤

ኘ) በፓርቲው ከፍተኛ የአመራር አካላት የሚወሰኑና በሀገሪቱና በሕዝቦቿ ላይ ጉልህ ተጽዕኖ የሚያሳርፉ ዐቋሞችና ውሳኔዎች ሁሉ ውሳኔውን ባስተላለፈው አካል በምሥጢር ተጠብቆ እንዲቆይ ካልተወሰነ በስተቀር ከአስፈላጊው ማብራሪያ ጋር ለአባላትና እንደአስፈላጊነቱ ለሕዝብ ይገለጻሉ፤

አ) በፓርቲው ጉባኤዎች፤ ኮንፈረንሶችና ስብሰባዎች የሚተላለፉ ውሳኔዎች እና አቅጣጫዎች በቃለ ጉባኤ ተይዘው፣ ጸድቀው ይቀመጣሉ፤

ከ) በልዩ ሁኔታ በምሥጢርነት ተጠብቀው ሊቆዩ የሚችሉ የፓርቲ ጉዳዮች የሚለዩበት አሠራር ይዘረጋል፤

ኸ) በየደረጃው የሚገኙ የፓርቲ አመራር አካላት ለወሰኗቸው ውሳኔዎች በተናጠልና በጋራ በሙሉ ኃላፊነት ይወስዳሉ። በተጨማሪም ኃላፊነትን ያለመወጣት ወይም ከተሰጠ ኃላፊነት ውጪ መሥማራት ተጠያቂነትን ያስከትላል፤

ወ) ተጠያቂነትም እንደሁኔታው በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ ወይም በሀገሪቱ ሕጎች መሰረት ፖለቲካዊ፤ አስተዳደራዊ ወይም ሕጋዊ ርምጃዎችን ያስወስዳል፤

ዐ) በየደረጃው የሚገኙ የፓርቲው አካላት የሥራ እንቅስቃሴያቸውን የሚያሳይ ዝርዝር ዕቅድና ሪፖርት በወቅቱ የማቅረብ ኃላፊነት አለባቸው፤ የበላይ አካላትም ወቅታዊ ግብረ-መልስ መስጠት አለባቸው፤

ዘ) አባላትና አደረጃጀቶች የሥራ አፈጻጸም ውጤታማነታቸውን የሚመዘኑባቸውና እርስ በርስ የሚማማሩባቸው መደበኛ የውይይት ጊዜያት ይኖራቸዋል፤

ዠ) ፓርቲው አባላቱ፣ አመራሩና መዋቅሩ ላሳዩት የላቀ አፈጻጸም፣ የተሻለ አስተዋጽኦ ላበረከቱ፣ ለህዝብ የጎላ ፋይዳ ያላቸውን ተግባራት ላከናወኑ እና ረዘም ላለ ጊዜ በፓርቲ ውስጥ የላቀ ተግባር ለፈጸሙ አባላት እውቅናና ሽልማት ይሰጣል፡፡ ዝርዝር መመሪያው በብልፅግና ምክር ቤት ይወጣል፡፡

የ) ፓርቲው በሁሉም ደረጃዎች የወጣቶችና የሴቶች ክንፎችን የማሳተፍና የማብቃት አቅጣጫና አሠራርን ይከተላል፤

ደ) ፓርቲው ከሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር የሚኖረው ግንኙነቶች በሀገር አቀፍ ደረጃ ላሉት በማዕከላዊነት የሚወሰን ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ ከዚያ በታች ባሉት የፓርቲው አደረጃጀት ተፈጻሚ ሊሆን ይችላል፤

ጀ) ልዩ ድጋፍ የሚሹና አነስተኛ ቁጥር ያላቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች የፓርቲው አባላትና አደረጃጀቶች በየደረጃው ተገቢውን ውክልና እንዲያገኙና የአዎንታዊ እርምጃ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል። ዝርዝር መመሪያ በብልፅግና ምክር ቤት የሚወጣ ይሆናል፤

ገ) የፓርቲው ዓላማዎች፣ ፕሮግራምና ዕቅድ ተግባራዊ የሚሆኑት በፓርቲው ዋና ጽ/ቤት እንዲሁም በክልል፣ በአካባቢ የፓርቲ ጽ/ቤቶች የፓርቲ አደረጃጀቶች እና በውጪ ሀገር በሚኖሩ የፓርቲው መዋቅሮች አማካኝነት ይሆናል፤

ጠ) በፓርቲው አባላትና ዕጩ አባላት በሚፈጸሙ ጥፋቶች ላይ የሚወሰደው የዲስፕሊን እርምጃ የፓርቲውን ሥነ ምግባር ለማዳበር፣ ስሕተቶችንና ጉድለቶችን ለማረምና የፓርቲውን ጥራትና ጥንካሬ ለመጠበቅ የሚያገለግል ሊሆን ይገባል።

## አንቀጽ ዘጠኝ - <u>የፓርቲው ምርጫ መርህና የአሠራር ሥርዓት</u>

1. የፓርቲው የብልፅግና ምክር ቤት አባላት፣ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት፣ የፕሬዝዳንት፣ የምክትል ፕሬዝዳንቶች እና የኢንስፔክሽንና ሥነ-ምግባር ኮሚሽን አባላት፣ ዋና ኮሚሽነር፣ ምክትል ዋና ኮሚሽነር እና ዋና ጸሐፊ አመራር ምርጫ ግልጽ፣ ነጻና ፍትሐዊ በሆነ ሁኔታ በምሥጢር በሚሰጥ ድምፅ የሚመረጡ ይሆናል።
2. በፓርቲው ውስጥ በኃላፊነት ቦታዎች የሚደረጉ ምርጫዎች የጾታ ተዋጽኦን የጠበቁ መሆን ይኖርባቸዋል።
3. ማንኛውም የፓርቲ አባል በዚህ ደንብ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ (8)(ሠ) በወጣው የፓርቲ የምርጫ የአሠራር ሥርዓት መሠረት በሀገሪቱ በሚካሄዱ የጠቅላላ፣ የአካባቢ፣ የማሟያና የድጋሚ ምርጫዎች ፓርቲውን ወክሎ የመወዳደር መብት አለው።
4. በጠቅላላ፣ የአከባቢ፣ የማሟያ እና የድጋሚ ምርጫዎች በየደረጃው የሚገኘው የፓርቲ አባላት፣ አመራርና መዋቅሮች ሚና የብልፅግና ምክር ቤት በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ይወሰናል።፡
5. የፓርቲው ፕሬዝዳንትና ምክትል ፕሬዝዳንቶች ምርጫ በአስመራጭ ኮሚቴ ይከናወናል፡፡
6. የአስመራጭ ኮሚቴ አባላት የሚመረጡበት ሂደት እንደሚከተለው ይሆናል፤

    **ሀ)** የአስመራጭ ኮሚቴ ምርጫ ግልጽ፣ ነጻ፣ ዴሞክራሲያዊ፣ አካታችና የጾታ ተዋጽኦን በጠበቀ

መንገድ በድምጽ ከሚሳተፉ ጉባዔተኞች በፕሬዚዲየም አባላት አማካይነት የሚመረጡ ይሆናል፡

**ለ)** ለአስመራጭ ኮሚቴ ከጉባኤተኛው ሰባት እጩ አባላት በጥቆማ ቀርበው አምስቱ ባገኙት የድምጽ መጠን መሰረት የሚመረጡ ይሆናል፤

**ሐ)** ለአስመራጭ ኮሚቴ በእጩነት የሚቀርቡትን እያንዳንዱን አባላት ቢያንስ በሁለት ተሳታፊዎች የግምገማ አስተያየት ሊሰጥባቸው ይገባል፤

**መ)** በእያንዳንዱ የአስመራጭ ኮሚቴ አባላት እጩዎቹ ላይ የድጋፍ፣ የተቃውሞ እና ድምጸ ተዓቅቦ ድምጽ በጉባኤተኛው ሊቀርብባቸው ይገባል፤

**ሠ)** ለአስመራጭ ኮሚቴ እጩ ሆኖ የቀረበው አባል አንድ ሶስተኛ የድጋፍ ድምጽ ካገኘ ለውድድር የሚቀርብ ይሆናል፡፡

**ረ)** ለአስመራጭ ኮሚቴ የሚመረጡት አባላት በፓርቲው ሲነየር የሆኑና ልምድ ያላቸው፣ የብሄርንና የጾታን ስብጥር ያማከለ፣ የምርጫ ስራውን በመልካም ዲሲፒሊን ሊያሳኩ የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡

**ሰ)** የተመረጡት አምስቱ የአስመራጭ ኮሚቴ አባላት ከመካከላቸው ሰብሳቢና ፀሃፊን በመሰየም ለጉባኤተኛው ያሳውቃሉ፡፡

7. የአስመራጭ ኮሚቴው የሚከተሉት ተግባራት እና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡
   ሀ) የፓርቲውን ፕሬዝደንት እና ምክትል ፕሬዝደንቶችን ያስመርጣል፤
   ለ) የምርጫውን ውጤት መሰረት በማድረግ ተመራጭ ፕሬዝደንት እና ምክትል ፕሬዝደንቶችን ለጉባኤተኛ ያሳውቃል፤
   ሐ) የአስመራጭ ኮሚቴው ተመራጩ ፕሬዝዳንት እና ምክትል ፕሬዝደንቶች ወደ መድረክ መጥተው እንዲሰየሙ ያደርጋል፡፡
   መ) ከዚህ ተግባር በኋላ የአስመራጭ ኮሚቴ የስልጣን ቆይታ የሚያበቃ ይሆናል፡፡
8. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተደነገገው መሰረት የሚስጢር ድምጽ አሰጣጥ፣ ድምጽ ቆጠራ፣ ዉጤት መደመር፣ ውጤት አገላለጽ ሂደቶች በቴክኖሎጂ በታገዘ የሚስጢር ድምጽ አሰጣጥ ጥቅም ላይ ይውላል፤
9. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (8) የተደነገገው ቢኖርም ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ዕክል በሚያጋጥምበት ጊዜ በኮሮጆ የሚስጢር ድምጽ አሰጣጥ ዘዴ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

## <u>ምእራፍ ሁለት</u>

## <u>አባልነት</u>

**አንቀጽ አስር - <u>የፓርቲው አባል ስለመሆን</u>**

1. ከዚህ በታች የተመለከቱትን መመዘኛዎች የሚያሟላ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ የፓርቲው አባል መሆን ይችላል።

   ሀ) የፓርቲውን ፕሮግራምና መተዳደሪያ ደንብ ተቀብሎ በጽናት ተግባራዊ ለማድረግ ፍቃደኛ የሆነ፤

   ለ) መልካም ሥነ-ምግባር ያለውና በኅብረተሰቡ ውስጥ ተቀባይነት ያለው፤

   ሐ) በኅብረ ብሔራዊነት እና በሀገራዊ አንድነት ላይ ጽኑ አቋም ያለውና ዋልታ-ረገጥ አመለካከትና ተግባሮችን በጽናት የሚታገል፤

   መ) ዜጎችንና ሕዝቦችን በእኩልነት የሚያገለግል፣ የሕዝብ ጥቅምን የሚያስቀድም፣ከሙስናና ብልሹ አሠራሮች ራሱን ያራቀና ሌሎችንም የሚታገል፤

   ሠ) የፓርቲውን ዕሴቶችና ዓላማዎችን ተቀብሎ የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣት ቁርጠኛ የሆነ፤

   ረ) ወርኃዊ የአባልነት ክፍያ ለመክፈል ፍቃደኛ የሆነ፤

   ሰ) እድሜ 18 ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆነ፤

   ሸ) የሌላ ፖለቲካ ፓርቲ አባል ያልሆነ፤

   ቀ) የፖለቲካ ፓርቲ አባል የመሆን መብቱ በሕግ ያልተገደበ ወይም በፍርድ ቤት ውሳኔ ያልተገፈፈ፤

   በ) በዚህ ደንብ በተወሰነው መሠረት የሙከራ ጊዜውን የጨረሰ የፓርቲው አባል መሆን ይችላል።

2. የአባልነት የዕድሜ ጣሪያን እና የክብር አባልነትን የተመለከተ ዝርዝር አፈፃፀም መመሪያ በብልፅግና ምክር ቤት ይወጣል።

**አንቀጽ አስራ አንድ - <u>ለአባልነት የሚቀርብ ጥያቄ</u>**

1. አንድ የፓርቲው አባል ለመሆን የወሰነ ዜጋ በሥራ ወይም በመኖሪያ አካባቢው ለሚገኘው ለብልፅግና ቤተሰብ ማመልከት ይኖርበታል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተቀመጠው እንደተጠበቀ ሆኖ በየደረጃው የሚገኝ የፓርቲው መዋቅርና አባል ለፓርቲው ፕሮግራምና መተደደሪያ ደንብ ታማኝና ለተግባራዊነቱም ይታገላል ብሎ ያመነበትን ግለሰብ ለፓርቲው አባልነት ሊመለምለው ይችላል።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) መሠረት መስፈርቱን አሟልቶ የተመለመለ ግለሰብ ለስድስት ወራት በደጋፊ አባልነት እና ለስድስት ወር በዕጩ አባልነት መቆየት አለበት።

4. የፓርቲው የብልፅግና ቤተሰብ የአንድ ደጋፊ አባል ወደ እጩ አባል እንዲሻገር ቀርቦ፣ የማጽደቅ ወይም በደጋፊ አባልነት እንዲቆይ በብልፅግና ህብረት የአባላት ኮንፈረንስ የውሳኔ ሐሳብ ቀርቦ መጽደቅ ይኖርበታል። በብልፅግና ህብረት ውሳኔ ቅሬታ ያለው ደጋፊ አባል አንድ ደረጃ ከፍ ብሎ ለሚገኘው ፓርቲ አደረጃጀት ቅሬታ ማቅረብ ይችላል።

5. በፓርቲው የብልፅግና ቤተሰብ የአንድ እጩ አባል አፈጻጸም ታይቶ ወደ ሙሉ አባል እንዲሻገር ቀርቦ፣ የማጽደቅ ወይም ተጨማሪ ከሦስት ወራት ላልበለጠ ጊዜ የዕጩነት ቆይታ እንዲራዘም ለብልፅግና ህብረት የአባላት ኮንፈረንስ የውሳኔ ሐሳብ አቅርቦ ያፀድቃል። በብልፅግና ህብረት ውሳኔ ቅሬታ ያለው ዕጩ አባል አንድ ደረጃ ከፍ ብሎ ለሚገኘው ፓርቲ አደረጃጀት ቅሬታ ማቅረብ ይችላል።

6. ዕጩ የሆነው አባል የፓርቲውን ፕሮግራም፣ መተዳደሪያ ደንብ እና የፓርቲውን የዲሲፕሊን መመሪያ አውቆ ከተቀበለ በኋላ በአባላት ኮንፈረንስ ፊት ቃለ-መሃላ ይፈጽማል፡፡

7. የዕጩ አባልነት ቆይታ ከአንድ ጊዜ በላይ አይራዘምም፤ ከክትትል ሂደትም ይሰረዛል።

8. ደጋፊ እና ዕጩ አባላት በሙከራ ጊዜ ቆይታቸው ፓርቲው የሚሰጠውን ተልዕኮ ይፈጽማሉ።

9. የአባላትና አመራር ምልመላ፣ ግንባታ፣ ምደባ፣ ምዘናና ስንብት ዝርዝር መመሪያ በፓርቲው ብልፅግና ምክር ቤት ይወጣል።

**አንቀጽ አሥራ ሁለት - <u>የአባል መብት</u>**

1. ማንኛውም የፓርቲ ሙሉ አባል የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፡-

   ሀ) በፓርቲው አካላት ምርጫዎች የመምረጥና የመመረጥ፤

   ለ) በፓርቲው ጉባኤዎች የመሳተፍ፣ በውይይት የመካፈልና በድምፅ በሚወሰኑ ጉዳዮች ላይ ድምፅ የመስጠት፣ በማንኛውም ጉዳይ ላይ በሕጋዊ መድረኮች ሐሳቡን በጽሑፍም ሆነ በቃል የማቅረብ፤

   ሐ) በማንኛውንም የፓርቲ አካል ወይም አባላት ላይ በመረጃ የተደገፈ ገንቢ ሂስ የማቅረብ፤

መ) በየትኛውም የፓርቲ ውሳኔ ቅር ከተሰኘ ቅሬታውን በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት በየደረጃው ለሚመለከተው አካል የማቅረብ፤

ሠ) ስለራሱ፣ ስለአካል፣ ስለፓርቲው ማወቅ የሚገባውን ነገር እስከ ፓርቲው የብልፅግና ምክር ቤት የመጠየቅና መልስ የማግኘት፤

ረ) የፓርቲውን መተዳደሪያ ደንብ፣ ፕሮግራም፣ አቋሞችና ውሳኔዎች ለሌሎች የማሳወቅ፤ የማስተዋወቅ፤ የማሥረጽና በተጨባጭ እንዲተገበር የማድረግ እና፤

ሰ) በየትኛውም ጊዜ በጽሑፍ አመልክቶ እና በእጀቹ የሚገኙ የፓርቲው ንብረቶችን ኃላፊነት በተሞላበት አግባብ አስረክቦ ከአባልነት መልቀቅ ይችላል።

ሸ) የአባልነት መታወቂያ የማግኘት መብት አለው፡፡

2. ማንኛውም ዕጩ አባል በየደረጃው ለፓርቲው አካላት የመምረጥና የመመረጥ እንዲሁም ድምፅ የመስጠት መብት የለውም፣ የሌሎች የአባልነት መብቶች ግን ተጠቃሚ ነው፤ የግዴታዎችም ተገዥ ይሆናል።

3. የፓርቲ አባላት በክብር የሚሸኙበት፣ በክብር እና በፍቃደኝነት የተሰናበቱ አባላትን ፓርቲው ልምዳቸውን የሚጠቀምበት የአሰራር ስርዓት በብልፅግና ምክር ቤት በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል።

## አንቀጽ አስራ ሶስት - <u>አባልነት ስለማቋረጥ</u>

ሀ) በራስ ፍላጎት፣

ለ) በክብር በመሰናበት፣

ሐ) በሞት፣

መ) የሌላ ፖለቲካ ፓርቲ አባል ሆኖ ከተገኘ፣

ሠ) በህግ መብቱ ሲገደብ፣

ሠ) በዲሲፕሊን ቅጣት ከአባልነት ይሰናበታል፡፡

## አንቀጽ ዐሥራ አራት - <u>የአባልነት ግዴታ</u>

ማንኛውም የፓርቲ አባል የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፡-

1. በማንኛውም ጊዜና በየትኛውም ቦታ በፓርቲ ሕግ መሠረት የጸደቁትን የፓርቲውን ፕሮግራም፣ መተዳደሪያ ደንብ፣ መመሪያዎች፣ ውሳኔዎችና ዕቅዶችን የማወቅ፣ የመቀበል፣ የማክበር፣ የመገዛት እና ለተግባራዊነታቸው በግንባር ቀደምትነት የመታገል፤
2. በሚገኝበት የሥራ መስክ እና ኃላፊነት ደረጃ የፓርቲውን አንድነት፣ ጥራትና ጥንካሬ፣ የፓርቲውን የፖለቲካ ዕሳቤዎች ለመጠበቅ ሙሉ ተሳትፎ የማድረግ፤
3. የፓርቲውን መርሆዎች፣ ዕሴቶችና የአባላትን የዲሲፕሊን ሕጎችን የማክበር እና የፓርቲውን የህዝብና የሀገርን ደኅንነትና ሉዓላዊነት የመጠበቅ፤
4. የሀገሪቱን ሕጎች እና ልዩ ልዩ መንግሥታዊ ውሳኔዎችን ማክበር፤
5. የፓርቲውን አንድነት፣ ጥራትና ጥንካሬ የሚጎዱ ማናቸውንም ዝንባሌዎችና ድርጊቶችን የማጋለጥና የመታገል፤
6. በፓርቲው ውስጥ በግለሰቦች ወይም በቡድኖች የተያዙ ተናጠል ዐቋሞችን የፓርቲው በማስመሰል በማናቸውም መልኩ በሚዲያ ማሠራጨት የተከለከለ መሆኑ፤
7. በአባላት መካከል የሚኖረውን መልካም ግንኙነት ከሚያጎድፍ ድርጊቶች የመታቀብ፤
8. በዚህ ደንብ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ (8)(ተ) እንደተገለጸው የብልፅግና ምክር ቤት በሚያወጣው የአባልነት መዋጮ ዓይነትና አከፋፈል መመሪያ መሠረት የአባልነት መዋጮ የመክፍል፤
9. የፓርቲውን ንብረት በአግባቡ የመጠበቅ፤
10. ከሙስና የጸዳ፣ ሙስናንና አድሎአዊ አሠራርን የመታገልና የማጋለጥ ግዴታ እና
11. ከአንድ አካባቢ ወይም የሥራ ቦታ ወደ ሌላ አካባቢ ወይም የሥራ ቦታ በቋሚነት ለቅቆ ሲሄድ የለቀቀበትን እና የደረሰበትን የፓርቲ መዋቅር ማሳወቅ፣ የፓርቲውን ንብረት እና ሰነዶችን ለለቀቀበት አካባቢ የፓርቲ መዋቅር ማስረከብ አለበት።

**አንቀጽ ዐሥራ አምስት - <u>በአባላት ላይ በዲሲፕሊን ጉድለት ስለሚወሰዱ እርምጃዎች</u>**

1. ማንኛውም የፓርቲ አባል እና አመራር በሚመለከተው የፓርቲ አካል የወጣ የዲሲፕሊን መመሪያ/ዎችን የማክበር ግዴታ አለበት፡፡
2. ማንኛውም አባል ወይም አመራር በሚከተሉት ሁኔታዎች ከተግሣጽ ጀምሮ ከአባልነት እስከ ማሰናበት የሚያደርስ እርምጃ ሊወሰድበት ይችላል፤

ሀ) የፓርቲውን ፕሮግራም፣ መተዳደሪያ ደንብ፣ ውሳኔዎችና መመሪያዎች ያላከበረ ወይም ሌሎች ጥፋቶችን የፈጸመ አባል ወይም ዕጩ አባል ጉዳዩ በዝርዝር ታይቶ እንደ ጥፋቱ ክብደት የዲስፕሊን እርምጃ ይወሰድበታል፣

ለ) ማንኛውም አባል የፓርቲውን የአባልነት መዋጮ በተከታታይ ለ6 ወራት አሳማኝ ባልሆነ ምክንያት ካልከፈለ እና ውዝፍ መዋጮውን ለመክፈል ፍቃደኛ ካልሆነ ከአባልነቱ በራሱ ፈቃድ እንደለቀቀ ይቆጠራል፤

ሐ) ማንኛውም አባል በትክክለኛ መረጃ ላይ ሳይመሠረት አባላትን ከመለመለ ወይም ከአባልነት እንዲሰረዝ ያደረገ፣ አባላትን ከወነጀለ በዲስፕሊን ጥፋት ይጠየቃል፤

መ) ማንኛውም አመራር ወይም አባል የሐሰት ሪፖርት መስጠትም ሆነ መጠቀም ክልክል ነው፤

ሠ) በፓርቲው ውስጥ አንጃነት እና ቡድንተኝነት መፍጠር ወይም ማስፋፋት ክልክል ነው፤

ረ) ማንኛውም አባል የሌላ ፖለቲካ ፓርቲ አባል መሆኑ ከተደረሰበት ከፓርቲ አባልነቱ ይሰረዛል፤

ሰ) ከላይ የተዘረዘሩት እንደተጠበቁ ሆነው በአገሪቱ ህጎች ጥፋት ተብለው የሚቆጠሩ ድርጊቶችን ፈፅሞ የተገኘ መሆኑ ሲረጋገጥ በፓርቲው አሠራርም ተጠያቂ ይሆናል፤

ሸ) የፓርቲው አባላትና ዕጩ አባላት የሚፈጽሟቸው ጥፋቶች ክብደት እየታየ የሚከተሉት እርምጃዎች ይወሰዳሉ፡-

**2) ለሙሉ አባል፤**

ሀ) ተግሣጽ፤

ለ) የቃል ማስጠንቀቂያ መስጠት፤

ሐ) የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት፤

መ) ከኃላፊነት ማገድ፤

ሠ) ከኃላፊነት ዝቅ ማድረግ፤

ረ) ከኃላፊነት ማንሣት፤

ሠ) ከአባልነት ማገድ፤

ሸ) ከአባልነት መሠረዝ።

**3) ለዕጩ አባል፤**

ሀ) የዕጩ አባልነት ለአንድ የሙከራ ጊዜ ማራዘም፤

ለ) ከዕጩ አባልነት መሰረዝ።

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እርምጃ የተወሰደበት አባል ወይም ዕጩ አባል አቤቱታውን በየደረጃው ላለው የፓርቲ መዋቅር አቅርቦ በውሳኔው ካልረካ በየደረጃው ላለው የፓርቲ የኢንስፔክሽንና የሥነ-ምግባር ኮሚሽን አቤቱታ ሊያቀርብ ይችላል።

5) የአመራርና አባላት የዲሲፕሊን ጉደለት እርምጃ አወሳሰድና አፈፃፀም በዚህ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 25(6) (ሰ) መሰረት የብልፅግና ምክር ቤት በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይፈጸማል።

## ምእራፍ ሦስት

## የፓርቲው አወቃቀርና አደረጃጀት

**አንቀጽ ዐሥራ ስድሰት - የፓርቲ አወቃቀርና የአመራር አካላት**

1. የፓርቲው ድርጅታዊ አወቃቀር የሀገሪቱን ሕገ መንግሥታዊ ፌዴራላዊ አወቃቀር የተከተለ ነው። በዚሁ መሠረት የፓርቲው ድርጅታዊ አወቃቀር የሚከተሉት ናቸው:-

   ሀ) ፌዴራል፤

   ለ) ክልል/አዲስ አበባ ከተማ/ድሬዳዋ አስተዳደር፤

   ሐ) ዞን /ከተማ/ክፍለ ከተማ/ልዩ ወረዳ፤

   መ) ወረዳ/ከተማ/ክፍለ ከተማ፤

   ሠ) ቀበሌ ናቸው።

2. ፓርቲው የሚከተሉት ተቋማዊ መዋቅሮች ይኖሩታል:-

   ሀ) ጉባኤ፤

   ለ) የብልፅግና ምክር ቤት፤

   ሐ) ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ፤

   መ) የፌዴራልና የክልል የፓርቲ አመራሮች የጋራ መድረክ፤

   ሠ) ፕሬዝዳንት፤

   ረ) ምክትል ፕሬዝዳንቶች፤

   ሰ) ማዕከላዊ የኢንስፔክሽና የሥነ-ምግባር ኮሚሽን፤

   ሸ) የፓርቲው ዋና ጽሕፈት ቤት፤

   ቀ) የፓርቲው የክልል ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች፤

በ) የብልጽግና የሴቶች ክንፍ፤

ተ) የብልጽግና የወጣቶች ክንፍ፤

ቸ) የፓርቲው የብልፅግና ህብረት እና

ነ) የፓርቲው የብልፅግና ቤተሰብ ናቸው።

3. የፓርቲው የብልፅግና ህብረትና የብልፅግና ቤተሰብ አባላትና አመራር በሥራ ቦታቸው ወይም በመኖሪያ አከባቢያቸው ይቋቋማሉ።

**አንቀጽ ዐሥራ ሰባት - <u>የፓርቲው ጉባኤ፣ የክልል፣ አዲስ አበባና ድሬዳዋ፣ የዞን፣ የከተማ፣ የወረዳና የቀበሌ የኮንፈረንሶች አወቃቀር</u>**

1. የፓርቲው ጉባኤ በፌዴራል ደረጃ ይቋቋማል።
2. በክልል ደረጃ ክልላዊ ኮንፈረንስ እንዲሁም በየደረጃው ከዞን እስከ ቀበሌ ኮንፈረንሶች ሊዋቀሩ ይችላሉ።
3. በፌዴራል ተቋማት የሚገኙ የፓርቲ አባላት ኮንፈረንስ ይኖራል።
4. የኮንፈረንስ ውክልና የአባላት ቁጥር፣ የሕዝብ ብዛትና ብዝሃነትን ለማስተናገድ አነስተኛ የሕዝብ ብዛት ቁጥር ያላቸውን የብሔር ብሔረሰብና ሕዝቦች አባላት ውክልና ባረጋገጠ መልኩ ይዋቀራል።
5. በመደበኛ ጉባኤና በእያንዳንዱ ኮንፈረንስ ወቅት የሚመረጡ ጉባዔተኞች እና የኮንፈረንስ ተሳታፊዎች ብቃት ያላቸው አባላትን ያካተተ ይሆናል።

**አንቀጽ ዐሥራ ስምንት - የፓርቲው ጉባኤ**

1. የፓርቲው ጉባኤ የፓርቲው ከፍተኛ የአመራር አካል ነው።
2. የፓርቲው ጉባኤ መደበኛ ስብሰባ በየሁለት ዓመት ተኩል አንድ ጊዜ ይካሄዳል፣
3. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) በተደነገገው መሰረት መደበኛ ጉባዔውን መጥራት የማይቻልበት አስገዳጅ ሁኔታ ሲያጋጥም የብልፅግና ምክር ቤቱ እና በኮሚሽን በጋራ ስብሰባ በ50% + 1 ድምጽ ለ6 ወራት ማራዘም ይቻላል፡፡ ስለጉባዔው መራዘም በወቅቱ ለአባላት እንዲያውቁ መደረግ ይኖርበታል፣ ሆኖም ጉባዔውን ከ6 ወራት በላይ ማራዘም አይቻልም
4. ጉባዔው በፕሬዚዲየም ይመራል፣ የፕሬዚዲየሙ አባላት የፓርቲው ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንቶች ይሆናሉ፣
5. የፕሬዚዲየም አባላት የሚከተሉት ኃላፊነትና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

ሀ) ጉባኤው ነጻና ዴሞክራሲዊ በሆነ አግባብ እንዲካሄድ በጥብቅ ዲሲፕሊን ይመራል፤

ለ) ጉባዔው የሚመክርባቸውን አጀንዳዎች አቅርቦ ያፀድቃል፤ የጉባዔ ውይይትን ይመራል፤

ሐ) በጉባዔው በድምጽ በሚወሰኑ ጉዳዮች ላይ ድምጽ ያሰጣል፣

መ) በጉባዔው አጀንዳዎች ላይ በማወያየት የውሳኔ ሀሳቦችን ያሰጣል፤

ሠ) ጉባዔ የሚመራጡ የፓርቲ የብልፅግና ምክር ቤት አባላት እና የኢንስፔክሽንና የሥነ-ምግባር ኮሚሽን አባላት ምርጫ ጥቆማ ይቀበላል፣ ድምጽ ያሰጣል፣

ሰ) የምርጫ ውጤት ለጉባዔው ያሳውቃል፣ ያጸድቃል፣

ረ) አስመራጭ ኮሚቴን ከጉባኤተኞቹ መካከል ያስመርጣል፡፡

6. የጉባኤው ተሳታፊዎች ቁጥር ከ500 በላይ ሆኖ፤ ስብጥሩ የብልፅግና ምክር ቤት በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ልዩ ድጋፍ የሚሹና አነስተኛ የሕዝብ ቁጥር ያላቸውን የኅብረተሰብ ክፍሎች ውክልና እንዲያገኙና የአዎንታዊ እርምጃ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በሚያስችል መልኩ ይፈጸማል።

7. የፓርቲው የብልፅግና ምክር ቤት ቢያንስ በአንድ ሶስተኛ ድምፅ ብልጫ ሲወስን በማንኛውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል።

8. የፓርቲው ማዕከላዊ የኢንስፔክሽንና የሥነ-ምግባር ኮሚሽን የቋሚ ጉባኤ አባላት አንድ ሶስተኛ የድጋፍ ድምፅ ካገኘ አስቸኳይ ሰብሰባ እንዲጠራ ሊያደረግ ይችላል።

9. የፓርቲው ጉባኤ አስቸኳይ ስብሰባ ሲጠራ ቀድሞ በተካሄደው መደበኛ ጉባኤ የተካፈሉት ጉባኤተኞች በቀጥታ ይሳተፋሉ።

10. ለመደበኛ የፓርቲው ጉባኤ ከአባላቱ መካካል ቢያንስ ሁለት ሶስተኛው በስብሰባው ላይ ሲገኙ ምልዐተ ጉባኤ ይሆናል።

11. የአስቸካይ ጉባኤ ስብሰባ ምልዐተ ጉባኤ 50%+1 ነው።

12. የዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 እና 11 የተደነገገው ቢኖርም በማንኛውም ሁኔታ የጉባዔ ተሳታፊዎች ብዛት ከ500 ማነስ የለበትም፣

13. የፓርቲው የብልፅግና ምክር ቤት እና ማዕከላዊ የኢንስፔክሽና የሥነ-ምግባር ኮሚሽን አባላት በቀጥታ በጉባኤው ስብሰባ ይሳተፋሉ።

14. የፓርቲው ጉባኤ አባላት ውክልናና ተሳትፎ የሕዝብ ብዛት፣ የአባላትን ቁጥርና ብዝሃነትን መሠረት ያደረገ ሆኖ ዝርዝሩ የብልፅግና ምክር ቤት በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይወሰናል።

15. ለመደበኛ ጉባኤ እና አስቸኳይ ጉባኤ የጉባኤዎቹ ጊዜ፣ ቦታና አጀንዳዎችን አስቀድሞ በፓርቲው ዋና ጽሕፈት ቤት በኩል መገለጽ አለበት።

**አንቀጽ ዐሥራ ዘጠኝ - <u>የፓርቲው ጉባኤ ተግባርና ኃላፊነት</u>**

1. የፓርቲው ጉባኤ የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

   ሀ) የፓርቲውን ፕሮግራም፣ መተዳደሪያ ደንብ ያጸድቃል፣ ያሻሽላል፤

   ለ) ፓርቲው የሚመራባቸውን አጠቃላይ አቅጣጫዎችና ውሳኔዎች ያስቀምጣል፤

   ሐ) የብልፅግና ምክር ቤት እና የማዕከላዊ የኢንስፔክሽንና የሥነ-ምግባር ኮሚሽን አባላት ቁጥር ይወስናል፤

   መ) የብልፅግና ምክር ቤት እና የማዕከላዊ የኢንስፔክሽንና የሥነ-ምግባር ኮሚሽንና እንደአስፈላጊነቱ በሌሎች አካላት የሚቀርቡለትን ሪፖርቶችን ያዳምጣል፣ ይገመግማል፣ ያጸድቃል፤

   ሠ) ፓርቲው ከሌሎች ፓርቲዎች ጋር የሚያደርገውን የውሕደት ወይም የቅንጅት ወይም ግንባር የመፍጠር የውሳኔ ሐሳብ ያጸድቃል፤

   ረ) የብልፅግና ምክር ቤት እና የማዕከላዊ የኢንስፔክሽንና የሥነ-ምግባር ኮሚሽን አባላት ዕገዳና ስንብት ላይ ውሳኔ ይሰጣል፤

   ሸ) የፓርቲውን ስምና ዓርማ ያጸድቃል፣ ያሻሽላል፣ ይለውጣል፤

   ቀ) የብልፅግና ምክር ቤት አባላት፣ የኢንስፔክሽንና የሥነ-ምግባር ኮሚሽን አባላት፣ የፓርቲውን ፕሬዝዳንት እና ምክትል ፕሬዝዳንቶች ይመርጣል፤

   በ) ጉባኤው መደበኛ ሥራውን ከመጀመሩ በፊት በዝግጅት ኮሚቴ የሚቀርብለትን የጉባኤ ዝግጅት ሪፖርትና የስብሰባውን የሥነ-ሥርዓት ደንብ መርምሮ ያጸድቃል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ጉባኤው ከተግባርና ኃላፊነቱ በከፊል ለብልፅግና ምክር ቤት ውክልና ሊሰጥ ይችላል።

3. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (ቀ) ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንቶች በልዩ ልዩ ምክንያት ቢጎድል በብልፅግና ምክር ቤት ከሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ይተካል፣

**አንቀጽ ሃያ - <u>የፓርቲው የብልፅግና ምክር ቤት</u>**

1. የፓርቲው የብልፅግና ምክር ቤት ተጠሪነቱ ለፓርቲው ጉባኤ ሆኖ ከጉባኤ እስከ ጉባኤ ፓርቲውን የሚመራ ከፍተኛ አካል ነው።

2. በብልፅግና ምክር ቤት አባላት በቀጥታ በነጻና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ከጉባኤው አባላት በምሥጢር ድምፅ አሰጣጥ በሚመረጡ አባላት የሚመሠረት ነው።
3. የብልፅግና ምክር ቤት አባላት ብዛትና ስብጥር የሕዝብ ብዛትን፣ የአባላት ቁጥርን እና ብዝሃነትን መሠረት ያደረገ ሆኖ ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ በብልፅግና ምክር ቤት ይወጣል።
4. የብልፅግና ምክር ቤቱ በየስድስት ወሩ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፤ ሆኖም የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ካመነበት ወይም ከብልፅግና ምክር ቤት አባላት መካከል አንድ ሶስተኛ ያህሉ ሲጠይቁ ከዚህ ባነሰ ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል።
5. የብልፅግና ምክር ቤት ምልዐተ ጉባኤ ከአባላቱ ከ50%+1 የተገኙበት ይሆናል።
6. በብልፅግና ምክር ቤት የተላለፈ ማንኛውም ውሳኔ ከፓርቲው ማዕከላዊ የኢንስፔክሽን እና የሥነ-ምግባር ኮሚሽን ውጪ በሁሉም የፓርቲው መዋቅሮችና አካላት ተፈጻሚ ይሆናል።
7. የብልፅግና ምክር ቤት በፓርቲው ፕሬዝዳንት እና/ወይም በምክትል ፕሬዝዳንቶቹ በጋራ ይመራል።
8. የብልፅግና ምክር ቤት የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-
   ሀ) የፓርቲውን ፕሮግራምና መተዳደሪያ ደንብ፣ የጉባኤው ውሳኔዎች ሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤
   ለ) በፓርቲው ጉባኤ በሚቀመጠው አቅጣጫና ውሳኔዎች መሠረት ፓርቲውን በበላይነት ይመራል፣ የፓርቲውን አጠቃላይ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ አቅጣጫዎችና ዕቅዶችን እንዲሁም የማስፈጸሚያ መመሪያዎችን ያመነጫል፣ አፈጻጸማቸውን በየጊዜው ይገመግማል፤
   ሐ) የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴን ሪፖርት ያዳምጣል፣ ይገመግማል፣ ውሳኔ በሚሹ ነጥቦች ላይ ይወስናል፤
   መ) በፓርቲው ፕሬዝዳንት የተፈፀመን የስምምነት የውሳኔ ሐሳብ መርምሮ ያጸድቃል፤
   ሠ) የፓርቲውን የምርጫ የአሠራር ሥርዓት መመሪያ ያወጣል፤
   ረ) የምርጫ ስትራቴጅ ያጸድቃል፤ ለምርጫ የሚደረገውን ሂደት የሚመራ የምርጫ ኮሚቴ ያቋቁማል፤
   ሰ) አስፈላጊ የሆኑ የፓርቲ መዋቅሮችን ይዘረጋል፤
   ሸ) የብልፅግና ምክር ቤት አባላት ስብጥር እና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላትን ቁጥርና ስብጥር ይወስናል፤

ቀ) ከአባላቱ መካከል የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላትን ይመርጣሉ፣ በልዩ ልዩ ምክንያት የተጓደሉትን ይተካል፣

በ) የብልፅግና ምክር ቤትን ዓመታዊ የሥራ ዕቅድና የፓርቲውን በጀት ያጸድቃል፤

ተ) የፓርቲ አባላት የመዋጮ ዓይነት፣ መጠንና አከፋፈል በተመለከተ መመሪያ ያወጣል፤

ቸ) በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ ትርጓሜ ላይ ለሚነሡ ክርክሮች ውሳኔ ይሰጣል፤

ነ) የፓርቲውን ፕሮግራምና መተዳደሪያ ደንብ ለማስፈጸም አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተግባራትን ሁሉ ያከናውናል፤

ኘ) ለፓርቲው ፕሮግራምና ደንብ ተገዢ ያልሆኑና የአመራር ብቃት የጎደላቸውን የብልፅግና ምክር ቤት አባላትን በሁለት ሶስተኛ ድምፅ ያግዳል፤

አ) በዚህ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 19(1)(ቀ) ከተመረጡ አካላት የሚቀርብ የመልቀቂያ ማመልካቻ ተቀብሎ ውሳኔ ይሰጣል፣

9. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (8) (ከሀ-አ) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የብልፅግና ምክር ቤቱ ከተግባርና ኃላፊነት በከፊል ለፓርቲው ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ውክልና ሊሰጥ ይችላል።

**አንቀጽ ሃያ አንድ - <u>የፓርቲው ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ</u>**

1. የፓርቲው የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለብልፅግና ምክር ቤቱ ሆኖ ከብልፅግና ምክር ቤት አባላት መካከል በምሥጢር ድምፅ ይመረጣል።
2. የሥራ አስፈጻሚው ኮሚቴ በፓርቲው ፕሬዝዳንት ይመራል።
3. የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ መደበኛ ስብሰባውን በሦስት ወር አንድ ጊዜ ያደርጋል።
4. የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አስቸኳይ ስብሰባ በፕሬዚዳንቱ ወይም ከሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት አንድ ሶስተኛ ያህሉ ከጠየቁ ከዚህ ባነሰ ጊዜ ሊጠራ ይችላል።
5. የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ምልዐተ ጉባኤ ከአባላቱ ከ50%+1 የተገኙበት ይሆናል።
6. የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

ሀ) በጉባኤውና በብልፅግና ምክር ቤት የሚወጡ ዕቅዶች፣ አቅጣጫዎች፣ ውሳኔዎችና መመሪያዎች መከበራቸውንና በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፣አመራር ይሰጣል፤

ለ) የጉባኤውንና የብልፅግና ምክር ቤት አቅጣጫዎችና ውሳኔዎች መሠረት በማድረግ የኅብረተሰቡ ኑሮ እንዲሻሻልና አንድ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ማኅበረሰብ ለመፍጠር እንዲቻል አስፈላጊውን ስልት ይቀይሳል፤ መመሪያ ይሰጣል፤ ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል፤

ሐ) ኅብረ ብሔራዊ አንድነታችንን የሚያጠናክርና የፌዴራል ሥርዓቱን የሚያጎለብት ሐሳቦችን ያመነጫል፤ መተግበራቸውን ይከታተላል፤

መ) የጉባኤውንና የብልፅግና ምክር ቤት ውሳኔዎች መተዳደሪያ ደንቡን መሠረት በማድረግ የፓርቲውን የውስጠ ፓርቲ ዴሞክራሲ የበለጠ ለማዳበር የሚያስችሉ መመሪያዎችን ከማዕከላዊ የኢንስፔክሽን እና የሥነ-ምግባር ኮሚሽን ጋር በመመካከር ያወጣል፤ ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል፤

ሠ) ለብልፅግና ምክር ቤት የሥራ ዕቅድና ሪፖርት ያቀርባል፤

ረ) በየደረጃው የሚገኙ የፓርቲ አመራር የሥራ እንቅስቃሴ ይመራል፤ ይከታተላል፤ይደግፋል፤

ሰ) ለፓርቲው ዋና ጽ/ቤት የዕለት ተዕለት የሥራ መመሪያ ይሰጣል፤

ሸ) የፓርቲ ጉባኤ አዘጋጅ ኮሚቴ ከብልፅግና ምክር ቤት፣ ከማዕከላዊ የኢንስፔክሽንና የሥነ-ምግባር ኮሚሽን እና ሌሎች አግባቢነት ካላቸው አካላት በተውጣጣ አባላት ያዋቅራል፡፡

ቀ) **የጉባኤ አዘጋጅ ኮሚቴ የሚከተሉት ተግባራት እና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፤**

1) የጉባኤው ስብሰባ ከመጀመሩ በፊት በብልጽግና ፓርቲ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 8 መሰረት ምልአተ ጉባኤ መሟላቱን ያረጋግጣል፤

2) የተገኙ የጉባዔ ተሳታፊዎችን እንዲመዘገብና ፊርማ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

3) ለጉባዔው የጉባኤ ዝግጅት ሪፖርት ያቀርባል፤ ያጸድቃል፡፡

4) የሁለተኛው ጉባኤ የስብሰባ የሥነ ሥርዓት ደንብ ለጉባዔው አቅርቦ ያጸድቃል፡፡

5) የፕሬዚዲየም አባላት በጉባዔው እንዲሰየሙ ያደርጋል፤

በ) የብልፅግና ምክር ቤት አጀንዳ ያዘጋጃል፤

ተ) የፓርቲው ፕሮግራም፣ አቅጣጫዎችና ውሳኔዎች ለፓርቲው አባላት እና ለመላው ሕዝብ ተደራሽ እንዲሆኑ ስልት ይቀይሳል ተግባራዊ መሆኑንም ያረጋግጣል።

7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) (ከሀ-በ) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ከተግባርና ኃላፊነቱ በከፊል ለፓርቲው ፕሬዝዳንት ውክልና ሊሰጥ ይችላል።

አንቀጽ ሃያ ሁለት - <u>የፌዴራልና የክልል ፓርቲ አመራሮች የጋራ መድረክ</u>

1. የፌዴራልና የክልል ፓርቲ አመራሮች የጋራ መድረክ በፓርቲው ፕሬዝዳንት ወይም በፕሬዝዳንቱ የሚወከል ምክትል ፕሬዝዳንት የሚመራ ሆኖ፤ የፓርቲው ምክትል ፕሬዝዳንቶች፣ የክልል አስተባባሪ ኮሚቴ ሰብሳቢዎች፣ የክልል ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊዎችንና ሌሎች በፕሬዝዳንቱ እንዲሳተፉ የተመረጡ አመራሮችን በአባልነት ያቀፈ ይሆናል።
2. የጋራ መድረኩ ተጠሪነት ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ይሆናል።
3. የጋራ መድረኩ በየሁለት ወሩ እየተገናኘ በወቅታዊ አገራዊ ጉዳዮች ላይ ይመክራል።
4. የጋራ መድረኩ የክልል አስተባባሪ ኮሚቴ አባላትን ምደባን ያፀድቃል።
5. በፓርቲው ጉባዔ፣ በብልፅግና ምክር ቤት እና ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚቀመጡ አቅጣጫዎችን ያስፈፅማል፣ ይመራል።

አንቀጽ ሃያ ሶስት - <u>የፓርቲው ፕሬዝዳንት</u>

1.የፓርቲው ፕሬዝዳንት ተጠሪነቱ ለጉባዔ እና ለብልፅግና ምክር ቤት ሆኖ የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

ሀ) የብልፅግና ምክር ቤትና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሰብሰባዎችን በሰብሳቢነት ይመራል፣

ለ) የብልፅግና ምክር ቤትና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሥራዎችን ያስተባብራል ፤

ሐ) የብልፅግና ምክር ቤትና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ውሳኔዎችን ያስፈፅማል፤

መ) ፓርቲውን በመወከል ከተለያዩ አካላት ጋር የሥራ ግንኙነት ያደርጋል፤ስምምነቶችን ይፈርማል፤

ሠ) የሥራ ሪፖርቱን ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ያቀርባል፤

ረ) ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ስብሰባዎች አጀንዳ ያዘጋጃል፤

ሰ) በብልፅግና ምክር ቤት እና በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

አንቀጽ ሃያ አራት - <u>የፓርቲው ምክትል ፕሬዝዳንቶች</u>

1. ፓርቲው ሁለት ምክትል ፕሬዝዳንቶች ይኖሩታል።
2. ምክትል ፕሬዝዳንቶቹ ተጠሪነታቸው ለፕሬዝዳንቱ ሆኖ፤ የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖራቸዋል፡-

ሀ) ፕሬዝዳንቱ በማይኖርበት ጊዜ በፕሬዝዳንቱ የተወከለው ምክትል ፕሬዚዳንት ተክቶ ይሠራል፤

ለ) የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴና ፕሬዝዳንቱ በሚሰጧቸው የሥራ ስምሪት መሠረት ሥራቸውን ያከናውናሉ።

**አንቀጽ ሃያ አምስት - <u>የፓርቲው ማዕከላዊ የኢንስፔክሽንና የሥነ-ምግባር ኮሚሽን</u>**

1. የኢንስፔክሽንና ሥነ-ምግባር ኮሚሽን ከፓርቲው ጉባኤ በሚመረጡ አባላት ይዋቀራል፤ የኮሚሽኑ አባላት ብዛት በጉባኤው የሚወሰን ሆኖ የሕዝብ ብዛትና የአባላትን ቁጥር እንዲሁም አነስተኛ ቁጥር ያላቸውን የኅብረተሰብ ክፍሎችን ውክልና እንዲያገኙና የአዎንታዊ ርምጃ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በሚያስችል አግባብ እንዲዋቀር ይደረጋል፤ ዝርዝሩ ማዕከላዊ ኮሚቴ በሚያወጣው በመመሪያ ይወሰናል።
2. ኮሚሽኑ ተጠሪነቱ ለፓርቲው ጉባኤ ነው።
3. የኮሚሽኑ አባላት ከሥራቸው ጋር የሚያጋጭ የፓርቲ ምደባ አይሰጣቸውም።
4. ኮሚሽኑ ቋሚ ጽሕፈት ቤት ተሿሚ አመራሮችና ተሿሚ ያልሆኑ ባለሞያዎች ይኖሩታል።
5. ኮሚሽኑ በየደረጃው በሚገኙ የፓርቲ አደረጃጀት ጽሕፈት ቤቶች ያደራጃል፣ የራሱን መዋቅር ይዘረጋል፤ አሠራራቸውም የሚከተለው ይሆናል፡-
   ሀ) የክልልን እና የአካባቢ የኢንስፔክሽንና ሥነ-ምግባር ኮሚሽን አባላት በየደረጃው በሚካሄዱ ኮንፈረንሶች ይመረጣሉ። ኮንፈረንስ እስከሚካሄድ ባለው ጊዜ የኮሚሽኑ አባላት መጓደል ወይም አዲስ ማቋቋም ሲያጋጥም ኮሚሽኑ ከየደረጃው ፓርቲ አሰተባባሪ ኮሚቴ ጋር በመነጋገር ጊዜያዊ ምደባ ይሰጣል፤
   ለ) የክልል፣ የፌዴራል ተቋማት አደረጃጀት እና የአካባቢ የኢንስፔክሽንና ሥነ-ምግባር ኮሚሽኖች አንድ ደረጃ ከፍ ብሎ ለሚገኘው የኮሚሽኑ መዋቅር እና በትይዩ ለሚገኘው ኮንፈረንስ ተጠሪ ይሆናሉ፤
   ሐ) በፌደራልና በየደረጃው የሚኖሩ ክልላዊና አካባቢያዊ የኢንስፔክሽንና ሥነ-ምግባር ኮሚሽን መዋቅሮች ባሉበት ደረጃ ካለ የፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ ጋር በትብብር ይሠራሉ።
6. ኮሚሽኑ የሚከተሉት ተግባራት እና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-
   ሀ) ኮሚሽኑ የፓርቲውን መተዳደሪያ ደንብና መመሪያዎች በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፤
   ለ) የፓርቲውን የፖለቲካ ጥራት እና የሥነ-ምግባር ጤናማነት ለማረጋገጥ አስፈላጊውን ክትትል ያደርጋል፤

ሐ) የፓርቲው ገንዘብ፣ ንብረትና ሰነዶች በአግባቡ መጠበቃቸውን ቁጥጥር ያደርጋል፤ የፓርቲው አባላት መዋጮ በወቅቱና በትክክል መሰብሰቡን ይቆጣጠራል፤

መ) የፓርቲው አባላትና አካላት መብቶች እና ጥቅሞች መከበራቸውን ይከታተላል፤

ሠ) ከአባላት የሚቀርቡ አቤቱታዎችን ይቀበላል፤ ይመረምራል፤ የእርምት የውሳኔ ሐሳቡን ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ እና እንደአግባቡ በየደረጃው ላሉ የፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴዎች ያቀርባል፤

ረ) በኮሚሽኑ የሚቀርበውን የእርምት ሐሳብ የሥራ አስፈጻሚው ካልተቀበለው ለማዕከላዊ ኮሚቴው ይቀርባል፤ ማዕከላዊ ኮሚቴው በጉዳዩ ላይ የሚሰጠው ውሳኔ እስከ ጉባኤ ድረስ ተፈጻሚ ይሆናል። እንዲሁም በኮሚሽኑ የሚቀርበውን የእርምት ሐሳብ አስተባባሪ ኮሚቴ ካልተቀበለው ኮሚሽኑ አንድ እርከን ከፍ ብሎ ላለው የፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ ክስ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

ሰ) ዝርዝር የፓርቲ የዲሲፕሊን፣ የኢንስፔክሽንና ቁጥጥር መመሪያ በማርቀቅ ለፓርቲው ብልጽግና ምክር ቤት አቅርቦ ያጸድቃል፣ ተፈጻሚነቱን ይከታተል፤

ሸ) የፓርቲው አባላትና አካላት የፓርቲውን ሥነ-ምግባር ማክበራቸውን ይከታተላል፣ የፓርቲ አባላትና አመራር ሊኖራቸው የሚገባ የፓርቲ ሥነ-ምግባር ከፓርቲ ጽ/ቤቶች ጋር ግንዛቤ ይሰጣል፡፡

ቀ) ሙስና በፓርቲው ውስጥ ትግል ስለመደረጉ ይከታተላል፣ ያስተባብራል፣ የሙስና ጥፋቶች ሲፈጸሙ ተገቢውን የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ለሚመለከተው የፓርቲ አካላት ያቀርባል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፡፡

በ) የሙስናና ብልሹ አሰራሮች ዙሪያ ጥናቶችን ያደርጋል፣

ተ) በየደረጃው የሥነ-ምግባር ጥሰቶችን ይመረምራል፣ ተገቢውን የእርምት ርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

ነ) ከፓርቲው የፖለቲካ አስተባባሪ ኮሚቴዎች በሚሰጥ ተልዕኮ መሠረት አስፈላጊ ሆነው የተገኙ የምርመራ፣ የክትትል እና የቁጥጥር ሥራዎችን ይሠራል፤

ኘ) በፓርቲው አካላት መካከል ልዩነት ሲኖር ወይም ፓርቲውን የሚመለከቱና መጣራት የሚገባቸው ጉዳዮች ሲኖሩ፤ እንዲሁም በፓርቲው ብልፅግና ምክር ቤት ወይም የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በኩል ጥያቄ ሲቀርብለት እንደ አንድ ነጻ አጣሪ አካል ሆኖ ያገለግላል፤

የራሱን የውሳኔ ሀሳብ ያካተተ ሪፖርትም ለብልፅግና ምክር ቤት ወይም ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ያቀርባል፤

አ) ኮሚሽኑ በፓርቲው መተዳደሪያ ደንቡ የተሰጡትን ተግባራትና ኃላፊነቶች አስመልክቶ በየወቅቱ ኢንስፔክሽንና ልዩ ልዩ ጥናቶችን ያካሂዳል፡፡ የጥናቱን ግኝቶች ከውሳኔ ምክረ-ሐሳብ ጋር ለሚመለከታቸው የፓርቲ አካላት ያቀርባል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤

ከ) ኮሚሽኑ ለሥራ የሚያስፈልገውን ዓመታዊ በጀት በማዘጋጀት እንዲፀድቅ ለብልጽግና ምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲፀድቅ ያስተዳድራል፣ ይመራል፣

ወ) ለፓርቲው ፕሮግራም፣ መተዳደሪያ ደንብና ለኮሚሽኑ መመሪያ ተገዢ ያልሆኑ የኮሚሽን አባላትን በሁለት ሶስተኛ ድምፅ ያግዳል፤

ዘ) ስለሥራው አፈጻጸም በፌደራል ደረጃ ለፓርቲው ጉባኤ፣ እንዲሁም እንደግባብነቱ በክልል እና አካባቢያዊ መዋቅሮች አንድ ደረጃ ከፍ ብሎ ላለው ኮሚሽን እና ለኮንፈረንስ ሪፖርት ያቀርባሉ፤

ዠ) ይህንን መተዳደሪያ ደንብ መሠረት በማድረግ የኮሚሽኑን የውስጥ አሠራር መመሪያዎች ማውጣት ይችላል።

7. የክልልና የአካባቢ የኢንስፔክሽንና ሥነ-ምግባር ኮሚሽን ተግባርና ኃላፊነቶች በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (6) ሥር የተዘረዘሩት ይሆናሉ።

8. ኮሚሽኑ በየሦስት ወሩ መደበኛ ስበሰባውን ያካሄዳል።

9. ኮሚሽኑ የራሱን ዓመታዊ ዕቅዶች እያዘጋጀ ተግባራቱን ይመራል።

10. በመተዳደሪያ ደንቡ በተሰጡት ተግባራትና ኃላፊነቶች አስመልክቶ ኮሚሽኑ በየደረጃው ከሚገኘው የፓርቲ ጽ/ቤት ሥራ አመራር ኮሚቴ ጋር በየጊዜው በጋራ የሚወያዩበት መድረክ ይኖራል፣ የግንኙነት ጊዜውም የብልጽግና ምክር ቤት በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ይሆናል፡፡

11. ኮሚሽኑ ከመካከሉ ዋና ኮሚሽነር፣ ምክትል ዋና ኮሚሽነር እና ዋና ጸሐፊ መርጦ ለጉባዔው ያሳውቃል፣

12. የኮሚሽን ዋና ኮሚሽነርና ምክትል ዋና ኮሚሽነር በፓርቲው ብልጽግና ምክር ቤት ስብሰባ ያለ ድምጽ ይሳተፋል፣

**አንቀጽ ሃያ ስድስት - <u>የፓርቲው ዋና ጽ/ቤት</u>**

1. ጽሕፈት ቤቱ ተጠሪነቱ ለፕሬዝዳንቱ ሆኖ የፓርቲውን የፖለቲካ፣ የድርጅት፣ የሕዝብና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ይመራል፣ የጥናትና ምርምር ማዕከል ሆኖ ያገለግላል።
2. ጽሕፈት ቤቱ ኃላፊና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ኃላፊዎች ይኖሩታል።
3. ጽሕፈት ቤቱ በየወቅቱ ዕቅድና ሪፖርት አዘጋጅቶ ለፕሬዝዳንቱ ያቀርባል።
4. ዕጩ የክልል/ከተማ አስተዳዳር የፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ አባላትን ከየክልሉ/ከተማ አስተዳደሩ የፓርቲ አመራሮች ጋር በመሆን ከለየ በኋላ ከፕሬዝዳንቱ ጋር በመመካከር ለፌዴራልና ክልል ፓርቲ አመራሮች የጋራ መድረክ ለውሳኔ ያቀርባል፤ ዝርዝሩ የፓርቲ አመራሮች ምደባን በተመለከተ በብልጽግና ምክር ቤት በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል።
5. የዋናው ጽሕፈት ቤትንና የየደረጃውን የክልል ፓርቲ ጽሕፈት ቤቶችን ዝርዝር አሠራርን አስመልክቶ ለማዕከላዊ ኮሚቴ ረቂቅ መመሪያ ያቀርባል።
6. ጽሕፈት ቤቱ የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-
   ሀ) የፓርቲው ብልጽግና ምክር ቤት እና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ዕቅዶችንና ሌሎች በፕሬዝዳንቱ የሚሰጡ አቅጣጫዎችን መሠረት በማድረግ የፓርቲውን ሥራዎች ያቅዳል፣ ያስፈጽማል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤
   ለ) የፓርቲውን ገንዘብ፣ ንብረት እና ሰነዶች በበላይነት ያስተዳድራል፣ በጥንቃቄ እንዲያዙ እና በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፣ የፓርቲውን የሂሳብ መዛግብት እና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በየዓመቱ በውጪ የሂሳብ ባለሞያ ወይም ኦዲተር እንዲመረመሩ እና እንዲረጋገጡ ያደርጋል፤
   ሐ) የአባላት አደረጃጀት፣ የፖለቲካ ግንባታ፣ የሕዝብና ዓለም አቀፍ ግንኙነት፣ የጥናትና ምርምርና ሌሎች ተግባሮችን ይፈፅማል፤
   መ) በፕሬዝዳንቱ በሚሰጠው አቅጣጫ መሠረት ፓርቲውን ወክሎ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር የሥራ ግንኙነት ያደረጋል፤
   ሠ) ከፕሬዝዳንቱ ጋር በመመካከር የፓርቲውን ልሳን ዋና አዘጋጅ እና የቦርድ አባላትን ይሰይማል፤
   ረ) የጸደቀውን የፓርቲ በጀት ያስተዳድራል፤

ሰ) የፓርቲውን ፕሮግራም፣ አቅጣጫዎች፣ የሥራ አፈጻጸም እና ዕቅዶችን በሚዲያና በሕዝብ ግንኙነት መሣሪያዎች ለሕዝብ ያስተዋውቃል፤

ሸ) በፓርቲው ስም ውል ይዋዋላል፤ ይከሳል፤ ይከሰሳል፤

ቀ) በፓርቲው የሰው ኃይል አስተዳደር መመሪያ መሠረት የጽሕፈት ቤቱን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፤

በ) የፓርቲ ጉባኤ ቦታ፣ ጊዜና አጀንዳ አዘጋጅቶ ሲወሰን ለሚመለከተው ፓርቲ አደረጃጀት ያሳውቃል፤

ተ) በፓርቲው አማካሪ ጉባኤ ሥራዎችን ያስተባብራል፤

ቸ) በብልጽግና ምክር ቤት፣ በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ወይም በፕሬዚዳንቱ የሚሰጡ ሌሎች ሥራዎችን ያከናውናል።

7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) (ከሀ-ቸ) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መመሪያ እንዲዘጋጅላቸው የተመለከቱና ሌሎች ለሥራ አስፈላጊ የሆኑ ዝርዝር መመሪያዎችን በፓርቲው የአሰላሳይ ቡድን አማካኝነት በማስጠናት ለፕሬዚዳንቱ ያቀርባል።

8. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) (ከሀ-ቸ) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የፓርቲ ዋና ጽሕፈት ቤቱ ከተግባርና ኃላፊነቱ ለክልል፣ አዲስ አበባና ድሬዳዋ ፓርቲ ጽሕፈት ቤቶች በከፍል ውክልና ሊሰጥ ይችላል።

## <u>ምእራፍ አራት</u>

## <u>የፓርቲው የክልል አደረጃጀት</u>

### አንቀጽ ሃያ ሰባት - <u>የፓርቲ አደረጃጀትና አወቃቀር</u>

1. ለፓርቲው ዋና ጽሕፈት ቤት ተጠሪ የሆኑ፤ የክልል እና የሁለቱ ከተማ አስተዳደሮች ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች የክልል/የከተማ አስተዳደር ስያሜ በመያዝ እንደሚከተለው ተቋቁመዋል:-

ሀ) በኦሮሚያ ክልል የብልፅግና ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት፤

ለ) በአማራ ክልል የብልፅግና ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት፤

ሐ) በሶማሌ ክልል የብልፅግና ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት፤

መ) በትግራይ ክልል የብልፅግና ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት፤

ሠ) በአፋር ክልል የብልፅግና ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት፤

ረ) በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የብልፅግና ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት፤

ሰ) በጋምቤላ ክልል የብልፅግና ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት፤

ሸ) በሐረሪ ክልል የብልፅግና ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት፤

ቀ) በሲዳማ ክልል የብልፅግና ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት፤

በ) በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል የብልፅግና ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት፤

ቸ) በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የብልፅግና ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት፤

ነ) በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል የብልፅግና ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት፤

ኘ) በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የብልፅግና ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት፤

አ) በድሬዳዋ አስተዳደር የብልፅግና ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት።

2. ለክልል/ከተማ አስተዳደር ፓርቲ ጽሕፈት ቤት ተጠሪ የሆኑ የዞኖች/ክፍለ ከተሞች/ልዩ ወረዳዎች፣ የወረዳዎች፣ የከተሞች እና ቀበሌዎች ጽሕፈት ቤቶች ይኖሩታል።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተቋቋሙት ጽሕፈት ቤቶች በየደረጃው የፓርቲ ኮንፈረንስ፣ አስተባባሪ ኮሚቴዎች፣ ጽሕፈት ቤቶችና የኢንስፔክሽንና የሥነ-ምግባር ኮሚሽን ይኖሯቸዋል።
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከተዘረዘሩት የክልል ፓርቲ ጽሕፈት ቤቶች በተጨማሪ በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47 መሠረት በሚመሠረት ክልል ውስጥ ሁሉ ፓርቲው የክልል ጽሕፈት ቤት ይኖረዋል።
5. በየደረጃው ያሉ የፓርቲው መዋቅሮች በክልሉ ያሉ የፓርቲውን አባሎች በሙሉ የሚያሳትፉ እና የውህዳን ቡድኖችን ውክልና የሚያረጋግጡ ይሆናሉ።

## አንቀጽ ሃያ ስምንት - <u>የክልል፣ አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋና የፌዴራል ተቋማት ፓርቲ ኮንፈረንስ የአሠራር ሥርዓት</u>

1. በየደረጃው የሚካሄደው የፓርቲው ኮንፈረንሶች የፓርቲ አባላት ትልቁ የፖለቲካ ግንባታ መድረክ ሆነው ያገለግላሉ።
2. በየደረጃው ለሚካሄደው የፓርቲ ኮንፈረንሶች ውክልናና ስብጥር በአባላት ብዛት ይወሰናሉ።
3. የፓርቲው ኮንፈረንሶች በየደረጃው በሚገኘው የፓርቲው አሰተባባሪ ኮሚቴ ጠሪነት የሚሰበሰብ ሆኖ፤ የክልል/አዲስ አበባና ድሬዳዋ/ እና የፌዴራል ተቋማት የአባላት ኮንፈረንስ በዓመት አንድ

ጊዜ፤ የዞን፤ የወረዳ/ልዩ ወረዳና የከተማ ኮንፈረንሳቸውን በዓመት ሁለት ጊዜ፤ የቀበሌ እና የብልጽግና ህብረት ደግሞ በየሶስት ወሩ ኮንፈረንሶች እንዲሁም የብልፅግና ቤተሰብ በየወሩ ውይይት ያካሄዳሉ።

4. የአስተባባሪ ኮሚቴ እና የኢንስፔክሽንና የሥነ-ምግባር ኮሚሽን አባላት በቀጥታ በኮንፈረንስ ይሳተፋሉ፣
5. በየደረጃው የሚካሄዱ ኮንፈረንሶች በአስተባባሪ ኮሚቴ ሰብሳቢና ምክትል ሰብሳቢ ይመራል፤

**አንቀጽ ሃያ ዘጠኝ - <u>የፓርቲ ኮንፈረንስ ተግባርና ኃላፊነት</u>**

1. በየደረጃው የፓርቲው ፕሮግራምና መተዳደሪያ ደንብ በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን ያረጋግጣል።
2. የፓርቲው አቅጣጫዎች፣ ውሳኔዎችና ዕቅዶች በትክክል መተግበራቸውን ያረጋግጣል።
3. የአባላቱን የፖለቲካ ብቃት እንዲዳብር ያደርጋል።
4. በፓርቲው የጉባኤና የኮንፈረንስ ተሳትፎና ውክልና መመሪያ መሠረት ለፓርቲው ጉባኤ እና በየደረጃው ለሚካሄዱ ኮንፈረንሶች አባላትን ይወክላሉ።
5. በየደረጃው ከፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ እና ከኢንስፔክሽንና የሥነ-ምግባር ኮሚሽን የሚቀርብለትን ዕቅድና የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ያዳምጣል፣ ይገመግማል፣ ያጸድቃል።
6. በየደረጃው የሚገኙ የፓርቲ ኮንፈረንስ፣ የፓርቲው ጉባኤ፣ የፓርቲው ብልጽግና ምክር ቤት እና የፓርቲው ሥራ አስፈጻሚ የሚያስቀምጡትን አጠቃላይ አቅጣጫና ውሳኔን ባከበረ መልኩ እና ሀገራዊ የሆኑት የፓርቲው አደረጃጀቶች በሚሰጡት የአመራር ማዕቀፍ ውስጥ ባሉበት የአስተዳደር ቀጠና የፖለቲካ ሁኔታ ላይ ይወያያሉ፣ ይገመግማሉ፤

**አንቀጽ ሠላሳ - <u>የክልሎች፣ የአዲስ አበባና የድሬዳዋ እንዲሁም የፌዴራል ተቋማት የፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ</u>**

1. የክልሎች፣ የአዲስ አበባና የድሬዳዋ የፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለፓርቲው የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ይሆናል።
2. የፌዴራል ተቋማት አስተባባሪ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለፓርቲው ዋና ጽ/ቤት ይሆናል።
3. የዞን፤ የከተማ፣ የክፍለ ከተማ፣ ልዩ ወረዳ፣ ወረዳ/ከተማና ቀበሌ ፓርቲ ኮሚቴ አንድ ደረጃ ከፍ ብለው ለሚገኙት የፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴዎች ተጠሪ ይሆናሉ።

4. የክልል፣ አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋና የፌደራል ተቋማት አደረጃጀት የፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ ቢያንስ በየወሩ አንድ ጊዜ፣ የዞን፣ የወረዳ/ልዩ ወረዳ፣ ከተማ፣ የክፍለ ከተማና ቀበሌ በወር ሁለት ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋሉ።
5. በየደረጃው የሚገኙ የፓርቲው አስተባባሪ ኮሚቴዎች የሚከተሉትን ተግባርና ኃላፊነት ይኖራቸዋል፦
   ሀ) በቀጣናቸው የፓርቲ የፖለቲካና የድርጅት ሥራዎች በበላይነት ያስተባብራሉ፤
   ለ) ከፓርቲው የበላይ አካላት የሚተላለፉ ውሳኔዎችንና መመሪያዎችን በተግባር ያውላሉ፣ ለሥራው ዝርዝር የአፈጻጸም ፕሮግራም አውጥተው በሥራ ላይ ያውላሉ፤
   ሐ) የፓርቲ መተዳደሪያ ደንብና መመሪያዎች በአግባቡ ስራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣሉ፣
   መ) ስለ ሥራው ክንውን ቀጥሎ ላለው የፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ እና ትይዩ ለሚገኘው ኮንፈረንስ ሪፖርት ያቀርባሉ፤
   ሠ) በየደረጃው የሚገኙ የፓርቲ ኮንፈረንሶች የሚያስቀምጡት አቅጣጫ፣ የፓርቲው ጉባኤ፣ የፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ እና የፓርቲው ሥራ አስፈጻሚ የሚሰጡትን አመራር እና ውሳኔን ባከበረ መልኩ ተግባራዊ መሆናቸው ይከታተላሉ፤
   ረ) በሀገር አቀፍ ደረጃ ባሉ የፓርቲው መዋቅሮች የሚሰጡት አመራር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ክልላዊ እና አካባቢያዊ በሆኑ ጉዳዮች ሐሳብ ያመነጫሉ።
6. የክልልና አካባቢያዊ ፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ አባላት ቁጥር ስብጥርና ምደባ ብልጽግና ምክር ቤት በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይወሰናል።

**አንቀጽ ሠላሳ አንድ - <u>የየደረጃው ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች</u>**

1. የፓርቲው ጽሕፈት ቤቶቹ በየደረጃው የፓርቲው የፖለቲካ፣ የድርጅትና የሕዝብ ግንኙነት ማዕከል ሆነው ያገለግላሉ።
2. የጽሕፈት ቤቶቹ ተጠሪነት አንድ ደረጃ ከፍ ብለው ለሚገኙ የፓርቲ ጽሕፈት ቤቶች ይሆናል።
3. ጽሕፈት ቤቶቹ በፌዴራልና ክልል ፓርቲ አመራሮች የጋራ መድረክ ወይም በየደረጃው ባሉት የፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴዎች የሚሰየሙ ኃላፊና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ኃላፊዎች ሊኖራቸው ይችላል።
4. የፓርቲው ጽሕፈት ቤቶች የሚከተሉትን ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖራቸዋል፦

ሀ) የክልሉን/አዲስ አበባና ድሬዳዋ/ የፓርቲ የፖለቲካና የድርጅት ሥራዎች ያቅዳሉ፣ ያስፈጽማሉ፣ አፈጻጸሙን ይከታተላሉ፤

ለ) የፓርቲ አባላት ኮንፈረንስ ያስተባብራሉ፤

ሐ) የፓርቲውን ገንዘብ፣ ንብረትና ሰነዶች በበላይነት ያስተዳድራሉ፣ በጥንቃቄ እንዲያዙና በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋሉ፤

መ) የፓርቲው ብልጽግና ምክር ቤት በሚያወጣው መመሪያ በሚወሰነው ድርሻ መሰረት ከገቢያቸው ለዋና ጽህፈት ቤት ፈሰስ ያደርጋሉ፣

ሠ) የቅርንጫፍ /ጽህፈት ቤቱን የሂሳብ መዛግብት እና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በየወቅቱ በውስጥ ኦዲት እና የዓመቱ በውጭ ኦዲተር ያስመረምራሉ፡፡

ረ) የአባላት አደረጃጀት፣ የፖለቲካ ግንባታ፣ የሕዝብ ግንኙነትና ሌሎች ተግባሮችን ይፈጽማሉ፤

ሰ) በፓርቲው ዋና ጽሕፈት ቤት በሚሰጠው አቅጣጫ መሠረት ፓርቲውን ወክለው በየደረጃው ከሦስተኛ ወገኖች ጋር ግንኙነት ያደርጋሉ፤

ሸ) በፓርቲው ዋና ጽሕፈት ቤት በሚሰጠው አቅጣጫ መሠረት የፓርቲውን ፕሮግራም፣ አቅጣጫዎች፣ የሥራ አፈጻጸም እና ዕቅዶችን በሚዲያና በሕዝብ ግንኙነት መሣሪያዎች ለሕዝብ ያስተዋውቃሉ፤

ቀ) በፓርቲው የሰው ኃይል አስተዳደር መመሪያ መሠረት የጽሕፈት ቤቱን ሠራተኞች ይቀጥራሉ፤ ያስተዳድራሉ፤ ያሰናብታሉ፤

በ) የፓርቲ መተዳደሪያ ደንብና መመሪያዎች በስራ ላይ ያውላሉ፣ ለአባላትና ለአመራር ግንዛቤ ይፈጥራሉ፣ መከበራቸውን ይከታተላሉ፡፡

ቸ) በየደረጃው ባሉት የፓርቲ አደረጃጀቶች የሚሰጡ ሌሎች ተግባሮችን ያከናውናሉ፤

ነ) ጽሕፈት ቤቶቹ በየወቅቱ ዕቅድና ሪፖርት አዘጋጅተው በየደረጃው ላሉት አስተባባሪ ኮሚቴ እና የፓርቲ ጽሕፈት ቤቶች ሪፖርት ያቀርባሉ።

**አንቀጽ ሠላሳ ሁለት - <u>የብልጽግና ፓርቲ የሴቶች ክንፍ</u>**

1. የብልጽግና የሴቶች ክንፍ ዋነኛ ተልዕኮ በፓርቲው ውስጥም ሆነ ውጭ የሴቶች መብቶችና ፍትሐዊ ተጠቃሚነት እንዲረጋገጥ እና የኢትዮጵያ የሕዝቦቿን ሁለንተናዊ ብልጽግና ለማረጋገጥ ሴቶች የሚጠበቅባቸውን ሚና እንዲወጡ ለማስቻል የግንባር ቀደምትነት ሚና መጫወት ነው።

2. የሴቶችን ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ታሳትፎና ተጠቃሚነት ለማጎልበት የሴቶች የመታገያ መድረክና ድምፅ ሆኖ ያገለግላል።

3. ክንፉ የፓርቲ አባላት ምንጭና ተተኪ አመራር ማፍሪያ መድረክ በመሆኑ፤ የፓርቲ እሳቤዎች፣ ፕሮግራም፣ መተዳደሪያ ደንብና መመሪያዎች ተገዥ እና የማክበር ግዴታ አለባቸው፣ ክንፉ ፕሮግራም አይኖረውም፣

4. የብልጽግና ፓርቲ አባል የሆኑ ሴቶች የብልጽግና ፓርቲ የሴቶች ክንፍ አባል መሆን ይችላሉ።

5. የብልጽግና የሴቶች ክንፍ ከፓርቲው መተዳደሪያ ደንብና የአሠራር መመሪያዎች በማይቃረን ሁኔታ የራሱ መተዳደሪያ ደንብና አሠራር መመሪያዎች ይኖረዋል።

6. የብልጽግና የሴቶች ክንፍ በየደረጃው በሚገኙ የፓርቲው አደረጃጀት ትይዩ መዋቅሮች ይኖሩታል።

7. በየደረጃው የሚገኘው የፓርቲ የአመራር አደረጃጀት በትይዩ ለሚገኘው የብልጽግና የሴቶች ክንፍ አደረጃጀት የቅርብ አመራርና ድጋፍ መስጠት ይጠበቅበታል።

8. ከፓርቲው ሥራ አስፈጻሚ ውጭ ባሉ በየደረጃው የሚገኙ የብልጽግና የሴቶች ክንፍ የአመራር አደረጃጀቶች ኃላፊና ምክትል ኃላፊ በትይዩ በሚገኙ የፓርቲው የአመራር አደረጃጀቶች ስብሰባዎች ያለ ድምፅ ተሳታፊ ሊሆኑ ይችላሉ።

9. የፌዴራል ሴቶች ክንፍ ጉባኤ ከፓርቲው ዋና ጽ/ቤት ጋር በመመካከር ሊጉ ከፓርቲው ተቋማዊ መዋቅሮችና አመራር አካላት ጋር የሚኖርን የሥራ ግንኙነት በተመለከተ ረቂቅ መመሪያ አዘጋጅቶ እንዲፀድቅ ለፓርቲው ብልጽግና ምክር ቤት ያቀርባል።

**አንቀጽ ሠላሳ ሶስት - <u>የብልጽግና ፓርቲ የወጣቶች ክንፍ</u>**

1. የብልጽግና ወጣቶች ክንፍ ዋነኛ ተልእኮ የኢትዮጵያና የሕዝቦቿን ሁለንተናዊ ብልጽግና ለማረጋገጥ ወጣቶች የሚጠበቅባቸውን ወሳኝ ሚና እንዲወጡ ለማስቻል እና የወጣቶችን ተሳትፎና ተጠቃሚነትና ለማረጋገጥ የማስተባበርና የመሪነት ሚና መጫወት ነው።

2. የወጣቶችን ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ለማጎልበት የወጣቶች የመታገያ መድረክና ድምፅ ሆኖ ያገለግላል።

3. ክንፉ የፓርቲ አባላት ምንጭና ተተኪ አመራር ማፍሪያ መድረክ በመሆኑ፤ የፓርቲ እሳቤዎች፣ ፕሮግራም፣ መተዳደሪያ ደንብና መመሪያዎች ተገዥ እና የማክበር ግዴታ አለባቸው፣ ክንፉ ፕሮግራም አይኖረውም፣

4. ዕድሜው ከ14-35 ዓመት የሆኑ ኢትዮጵያዊ ዜጋ የብልጽግና ፓርቲ የወጣቶች ክንፍ አባል መሆን ይችላል። ዝርዝር አፈፃፀሙ የብልጽግና ፓርቲ የወጣቶች ክንፍ በሚያወጣው መሥፈርትና የአሠራር መመሪያ ይወሰናል።
5. ዕድሜው ከ18 ዓመት በላይ የሆነ የክንፉ አባል የፓርቲው አባል መሆን ይችላል።
6. የብልጽግና የወጣቶች ክንፍ ከፓርቲው መተዳደሪያ ደንብና የአሠራር መመሪያዎች በማይቃረን ሁኔታ የራሱ መተዳደሪያ ደንብና አሠራር መመሪያዎች ይኖረዋል።
7. የብልጽግና ወጣቶች ክንፍ በየደረጃው በሚገኙ የፓርቲው አደረጃጀት ትይዩ መዋቅሮች ይኖሩታል።
8. በየደረጃው የሚገኘው የፓርቲ የአመራር አደረጃጀት በትይዩ ለሚገኘው የብልጽግና የወጣቶች ክንፍ አደረጃጀት የቅርብ አመራርና ድጋፍ መስጠት ይጠበቅበታል።
9. ከፓርቲው ሥራ አስፈጻሚ ውጭ ባሉ በየደረጃው የሚገኙ የአመራር አደረጃጀቶች ኃላፊና ምክትል ኃላፊ በትይዩ በሚገኙ የፓርቲው የአመራር አደረጃጀቶች ስብሰባዎች ያለ ድምፅ ተሳታፊ ሊሆኑ ይችላሉ።
10. የፓርቲው ሙሉ አባል ያልሆነ የብልጽግና የወጣቶች ክንፍ አባል በምርጫ በሚያዙ የፓርቲው የሥራ ቦታዎች መወዳደር አይችልም፣ በልዩ ሁኔታ ካልተጋበዘ በስተቀር በፓርቲው የአባላት ወይም የአመራር ስብሰባዎች መሳተፍ አይችልም።
11. የፌዴራል ወጣቶች ክንፍ ጉባኤ ከፓርቲው ዋና ጽ/ቤት ጋር በመመካከር ክንፍ ከፓርቲው ተቋማዊ መዋቅሮችና አመራር አካላት ጋር የሚኖርን የሥራ ግንኙነት በተመለከተ ዝርዝር መመሪያ አዘጋጅቶ እንዲፀድቅ ለፓርቲው ብልጽግና ምክር ቤት ያቀርባል።

## ምእራፍ አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**አንቀጽ ሠላሳ አራት - የሥልጣን ዘመን**

1. የፓርቲው ፕሬዝዳንት እና ምክትል ፕሬዝዳንቶች የኃላፊነት ዘመን ጣራ 10 አመት ይሆናል፣ የሌሎች አመራሮች የኃላፊነት ዘመን ማዕከላዊ ኮሚቴው በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይወሰናል።
2. የአመራሮች የእድሜ ጣሪያ 65 ዓመት ይሆናል።

**አንቀጽ ሠላሳ አምስት - <u>የፓርቲው የፋይናንስ ምንጮች</u>**

የፓርቲው የፋይናንስ ምንጮች ከአባላት መዋጮ፣ በሀገሪቱ ሕግ መሠረት ከፓርቲው ደጋፊዎች እንዲሁም ከሌሎች ህጋዊ ምንጮች ይሆናል።

**አንቀጽ ሠላሳ ስድስት - <u>የፓርቲው የሀብት አስተዳደርና የሂሳብ መዛግብት የአሠራር ሥርዓት</u>**

1. የፓርቲው የሰው ሀብት፣ የፋይናንስ፣ ንብረት፣ የበጀት፣ የግዥ እና ሰነዶች አስተዳደር የብልጽግና ምክር ቤት በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የሚተዳደር ይሆናል።
2. የፓርቲ ሰነዶች በአግባቡ መጠበቅ አለባቸው፣
3. ፓርቲው የተሟሉና ትክክለኛ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፣ በውስጥና በውጭ ኦዲተር በየዓመቱ ያስመረምራል።
4. በፓርቲው ገንዘብና ንብረት ላይ የመወሰን ሥልጣን የብልጽግና ምክር ቤት ይሆናል፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) የተደነገገው ቢኖርም የብልጽግና ምክር ቤቱ ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ውክልና ሊሰጥ ይችላል።
6. *የክንፎች ፋይናንስ በፓርቲ የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓት ይመራል፡፡*

**አንቀጽ ሠላሳ ሰባት - <u>በፓርቲው ውስጥ የሚፈጠሩ አለመግባባቶች አፈታት ሥርዓት</u>**

1. በፓርቲው አካላት ውስጥ የሚፈጠሩ አለመግባባቶች በዚህ ደንብ ውስጥ በተደነገጉ የአሠራር ሥርዓቶች መፈታት አለባቸው።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት መፈታት ካልቻለ በሀገሪቱ የምርጫ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነ ምግባር ሕግና በሌሎች ሕጎች መሠረት ይፈታል።

**አንቀጽ ሠላሳ ስምንት - <u>የፓርቲው ውሕደት፣ ቅንጅት ወይም ግንባር የመፍጠር ሥርዓት</u>**

1. ፓርቲው ከሌሎች ፓርቲ ወይም ፓርቲዎች ጋር ውሕደት ወይም ቅንጅት ወይም ግንባር መፍጠር ይችላል።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ተፈጻሚ የሚሆነው በኢትዮጵያ የምርጫ፣የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነ ምግባር ዐዋጅ መሠረት መሆኑን የብልጽግና ምክር ቤት ያረጋግጣል።

3. የብልጽግና ምክር ቤት በኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነ ምግባር ዐዋጅ መሠረት መሆኑን ካረጋገጠና የውሕደት ወይም የቅንጅት ወይም ግንባር የመፍጠር የውሳኔ ሐሳቡን ከተቀበለው በኋላ ለፓርቲው ጉባኤ አቅርቦ ያጸድቃል።

**አንቀጽ ሠላሳ ዘጠኝ - <u>የፓርቲው መፍረስ</u>**

የፓርቲው ጉባኤ ቢያንስ በሦስት አራተኛ ድምፅ ፓርቲው እንዲፈርስ ሊወስን ይችላል።

**አንቀጽ አርባ - <u>የፓርቲው የአሰላሳይ ቡድን</u>**

1. ፓርቲው ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዓላማዎቹን ለማሳካት የተለያዩ ሞያ ያላቸውን ምሁራንና ታዋቂ ግለሰቦችን ያቀፈ የፓርቲው የአሰላሳይ ቡድን(Think tank) በፓርቲው ዋና ጽ/ቤት ሊቋቋም ይችላል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ከፓርቲ በክብር እና በፍቃደኝነት የተሰናበቱ አባላት የአሰላሳይ ቡድን አባል ሊሆኑ ይችላል፡፡
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በክልል የፓርቲ ጽ/ቤት ኃላፊ አቅራቢነት የክልል አስተባባሪ ኮሚቴዎች የአሰላሳይ ቡድን ሊያቋቁሙ ይችላሉ።
4. የፓርቲው የአሰላሳይ ቡድን የአሰራር ስርዓት በፓርቲ ዋና ጽ/ቤት ሊዘረጋላቸው ይችላል፤

**አንቀጽ አርባ አንድ - <u>የፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ የበላይነት</u>**

1. መተዳደሪያ ደንቡ የፓርቲው የበላይ ሕግ ስለሆነ በፓርቲው አካላትና አባላት ላይ አስገዳጅነት ይኖረዋል።
2. በመተዳዳሪያ ደንቡና በሌሎች የፓርቲ ሰነዶች መካከል ግጭት ሲያጋጥም የዚህ መተዳደሪያ ደንብ ድንጋጌዎች የበላይነት ይኖራቸዋል።
3. በጉባዔው በጸደቀው መተዳደሪያ ደንብ ቅጅ ወይም በብልፅግና ምክር ቤት በጸደቁት መመሪያዎች እና በተለያዩ የፓርቲ ቋንቋዎች በተተረጎሙ ሰነዶች መካከል ግጭት ሲፈጠር ለጉባዔው ወይም ለብልፅግና ምክር ቤት ቀርቦ የጸደቀው የሰነድ ቅጅ የበላይነት ይኖረዋል፡፡

**አንቀጽ አርባ ሁለት - <u>መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>**

በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ለተለያዩ አካላት የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የፓርቲው ብልጽግና ምክር ቤት ይህን ደንብ ሥራ ላይ ለማዋል የሚያግዙ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

**አንቀጽ አርባ ሶስት - <u>መተዳደሪያ ደንቡን ስለማሻሻል፣ መቀየር እና ስለመሻር</u>**

1. ይህን መተዳደሪያ ደንብ ሊያሻሽል፣ ሊቀይርና ሊሽር የሚችለው የፓርቲው ጉባኤ ብቻ ነው።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የመተዳደሪያ ደንቡ የማሻሻያ ሐሳብ ሊቀርብ የሚችለው:-
   ሀ) በፕሬዝዳንቱ፤ ወይም
   ለ) በብልጽግና ምክር ቤት አንድ ሶስተኛ ድምፅ ድጋፍ ሲያገኝ፤ ወይም
   ሐ) በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው አብላጫ ድምፅ ድጋፍ ሲያገኝ፤ ወይም
   መ) በማዕከላዊ የኢንስፔክሽንና የሥነ-ምግባር ኮሚሽን አባላት አንድ ሁለተኛ ድምፅ ድጋፍ ሲያገኝ ነው።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የቀረበ የማሻሻያ ሐሳብ ለፓርቲው ጉባኤ መቅረብ የሚችለው በብልጽግና ምክር ቤት በአብላጫ ድምፅ ድጋፍ ካገኘ ነው።
4. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (3) መሠረት በብልጽግና ምክር ቤት በቀረበው የማሻሻያ ሐሳብ ላይ የፓርቲው ጉባኤ በአብላጫ ድምፅ ከወሰነ መተዳደሪያ ደንቡ ይሻሻላል።
5. በብልጽግና ፓርቲ አንደኛ መደበኛ ጉባዔ ጸድቆ የነበረው የመተዳደሪያ ደንብ ተሽሮ በዚህ መተዳደሪያ ደንብ ተተክቷል፣

**አንቀጽ አርባ አራት - <u>መተዳደሪያ ደንቡ ስለሚጸናበት ሁኔታ</u>**

ይህ መተዳደሪያ ደንብ በብልጽግና ፓርቲ የመጀመሪያ ጉባኤ ከጸደቀበት ጥር ------/2017 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል።

**ጥር ....../2017 ዓ.ም.**
**የብልፅግና ፓርቲ ጉባዔ**
**አዲስ አበባ፤ኢትዮጵያ**